| | |
|---|---|
| ዐይነት ፤ | ንግግር ። |
| ርእስ ፤ | የመሠረታዊ ፡ ሰነድ ፡ ዕደሳ ፡ ማብራሪያ ። |
| ደራሲ ፤ | (ንግግር) |
| ዕለት ፤ | ሚያዝያ ፡ 2011 ፡ ዓ.ም. ። |
| ዝግጅት ፤ | ፍጹም ። |
| መጽሔት ፤ | "ሥልጡንሕዝብና" ፡ መዜንው ፣ ቊ 2011.001 ። |
| ማስታወሻ ፤ | |
| ማሳሰቢያ ፤ | ንግግሩ ፡ የተካኼደው ፡ በመስከረም ፡ 2010 ፡ ዓ.ም. ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፣ የኢንተርኔት ፡ መሥመራችን ፣ ከዚያም ፡ የመርበቢያችንና ፡ የእ-ጦማር ፡ ሒሳቦቻችን ፡ ተደራሽነት ፡ በመታጐሉ ፡ ምክንያት ፣ እስከ ፡ ሚያዝያ ፡ ወር ፡ 2011 ፡ ዓ.ም. ፡ ዘግይቶ ፣ የትንሣኤን ፡ በዓል ፡ ምክንያት ፡ በማድረግ ፣ በመጠኑ ፡ ተሻሽሎ ፡ ወጥቷል ። |

የኢትዮጵያውያን ፡ ሀገራዊ ፡ ሠልጡንሕዝባዊ ፡ አንድነት ።

# የመሠረታዊ ፡ ሰነድ ፡ ዕደሳ ፡ ማብራሪያ ።

የኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ ጊዜያዊ ፡ ፈጻሚ ፡ ምክር ፡ ጸሓፊ ፣

አቶ ፡ ወሌ ፡ ነጋ ፣

ከሠልጡንሕዝብና ፡ መዜንው ፡ ጋራ ፡ የተናገሩት ።

ሚያዝያ ፣ 2011 ፡ ዓ.ም. ።

***ሥልጡንሕዝብና ፡ መዜንው ፤*** *ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ መቼ ፡ ተመሠረተ ፧ ለምን ፡ ተመሠረተ ፧ እንዴትስ ፡ ተመሠረተ ፧*

**አቶ ፡ ወሌ ፡ ነጋ ፤** በመዠመሪያ ፣ መላውን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፣ እንኳን ፡ ለብርሃነ ፡ ትንሣኤው ፡ በሰላም ፡ አደረሰኽ ፡ እያልኹ ፡ መልካም ፡ ምኞቴን ፡ በኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ ስም ፡ በፍጹም ፡ ትሕትና ፡ አቀርብለታለኹ ።

ለ"ሠልጡንሕዝብና" ፡ መዜንውም ፣ ሥራውን ፡ ባዲስ ፡ ስልት ፡ በመቀጠሉ ፡ ደስታዬን ፡ እየገለጽኹ ፣ መልካም ፡ ምኞቴን ፡ እንዲሁ ፡ አቀርባለኹ ።

ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፣ ሐምሌ ፡ 1 ፡ ቀን ፡ 1967 ፡ ዓ.ም. ፣ እብሪታንያ ፡ መዲና ፣ ለንደን ፡ ላይ ፡ ተመሥርቷል ። ለምሥረታው ፡ ምክንያት ፡ የኾነው ፣ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ በ1966 ፡ ዓ.ም. ፡ በመላ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ያስፋፋው ፡ እግዚእናውን ፡ (ገዢነቱን) ፡ የማስከበር ፡ ሰላማዊ ፡ ንቅናቄው ፡ በወታደራዊው ፡ ደርግ ፡ ዐምባ ፡ ገነንነት ፡ ሲደናቀፍ ፣ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ዐይነተኞች ፡ አፈ ፡ ጉባኤዎች ፡ የላኩት ፡ የዐደራ ፡ ቃልና ፡ የሥልጣን ፡ ውክልና ፡ ነው ። ዝርዝር ፡ ታሪኩ ፡ በ"ሠልጡንሕዝብና" ፡ መዜንው ፣ ቊ.1983-001 ፡ በመጠኑ ፡ ተገልጿል ።

ባጭሩ ፡ ለማስታወስ ፡ ያኽል ፣ በ1966 ፡ ዓ.ም. ፣ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፣ ሀገራዊ ፡ እግዚእናውን ፡ ከንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ከቀዳማዊ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ ይዞታ ፡ ሲያስመልስ ፣ በርክክቡ ፡ መኻከል ፣ ላዲስ ፡ አበባ ፡ ሰጥታ ፡ ተሠይሞ ፡ የነበረው ፡ ወታደራዊ ፡ ደርግ ፣ የተውጣጣባቸውን ፡ ደንቦች ፡ አታሎ ፣ መንግሥታዊውን ፡ ኀይል ፡ በእጁ ፡ መናኛ ፡ በመቈጣጠሩ ፣ ደኀኛውን ፡ የሥልጡንሕዝብና ፡ (የ"ዴሞክራሲ") ፡ ጕዞ ፡ አጨናገፈ ። ንቅናቄውን ፡ በሀገር ፡ ውስጥ ፡ በሰላማዊ ፡ መንገድ ፡ መምራት ፡ ስላልተቻለ ፣ ከወታደራዊ ፡ ደርግ ፡ ማጕርጥ ፡ ውጭ ፡ የሚገኙ ፡ ዕውቅ ፡ ያገር ፡ አዋዮች ፡ ተደራጅተው ፣ በወካዮቻቸው ፡ ስም ፡ ሀገራዊውን ፡ ሥልጣን ፡ ከሀገር ፡ ውጭ ፡ ተሠይመው ፣ ንቅናቄውን ፡ እንዲመሩላቸው ፡ ወሰኑ ።



ሲ.ዤኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ (1910-2000 ፡ ዓ.ም) ፣
የኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ መሥራችና ፡ የጊዜያዊ ፡ ፈጻሚ ፡ ምክሩ ፡
የቀድሞ ፡ ሊቀ ፡ መንበር ፡ (1982-1999 ፡ ዓ.ም.) ።

እነዚሁ ፡ የሕዝብ ፡ ተወካዮች ፡ በ1966 ፡ ዓ.ም. ፡ መጨረሻና ፣ በ1967 ፡ ዓ.ም. ፡ ቀዳሚ ፡ መንፈቅ ፡ ላይ ፣ ጥብቅ ፡ የዐደራ ፡ መልእክታቸውን ፣ ነፍሳቸውን ፡


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፣ 2011 ፡ ዓ.ም. ።

ይማርና ፥ ለሊየተና ፡ ጄኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ (1910 ፡ ዓ.ም.–2000 ፡ ዓ.ም.) ፥ ወደ ፡ ነበሩበት ፡ መግሪብ ፡ ("ምሮኮ") ፥ ኋላም ፡ በስደት ፡ ወደ ፡ ኼዱበት ፡ ወደ ፡ ብሪታንያ ፡ አከታትለው ፡ ላኩላቸው ። በዐደራው ፡ መሠረት ፥ ሊየተና ፡ ጄኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፥ እቅርባቸው ፡ ከተገኙላቸው ፡ ጥቂት ፡ ያገር ፡ ልጆች ፡ ጋራ ፡ መክረውና ፡ ዘክረው ፥ የኢትዮጵያን ፡ ሕዝብ ፡ ያስተባብራል ፡ ብለው ፡ ባመኑበት ፡ በሥልጡንሕዝብና ፡ የርትዕ ፡ መሠረት ፡ ላይ ፡ አንድነቱን ፦

*"የኢትዮጵያውያን ፡ ሀገራዊ ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ አንድነት ፡ ኢ.ሀ.ሥ.አ."*

አሠኝተው ፥ ሐምሌ ፡ 1 ፡ ቀን ፡ 1967 ፡ ዓ.ም. ፡ አቋቋሙ ።

እዚህ ፡ ላይ ፡ እንደምናስተውለው ፥ ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ የተመሠረተው ፡ በኢትዮጵያ ፡ የሥልጣን ፡ ተገቢነት ፡ በነበራቸው ፡ የሕዝብ ፡ እንደራሴዎች ፡ ዐደራና ፡ ውክልና ፡ ነው ።

***ሥ.መ.*** *፤ ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ ከ"ኢትዮጵያውያን ፡ ዴሞክራሲያዊ ፡ ኅብረት ፡ – ፡ ኢ.ዴ.ኅ." ፡ ጋራ ፡ ምን ፡ ዐይነት ፡ ግንኙነት ፡ ነበረው ፨*

**ወ.ነ.** ፤ ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ እንደ ፡ ተቋቋመ ፥ በ1967 ፡ ዓ.ም. ፥ ሕዝባዊ ፡ አንድነታዊ ፡ አካሉ ፡ ገና ፡ ሳይሞላና ፡ ሳይደረጅ ፥ መሪዎቹንም ፡ በወግ ፡ ሳይሠይም ፥ የኢትዮጵያን ፡ ጥፋት ፡ የሚመኙ ፡ የውጭ ፡ ኀይሎች ፡ እመኻል ፡ ገብተው ፡ አንድነቱን ፡ በማወክ ፥ የተወሰኑ ፡ አባላት ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ ተሿሹመው ፡ *"ኢ.ዴ.ኅ"* ፡ በሚል ፡ ኅብረት ፡ ጐንደው ፡ ተለይተው ፥ አለጊዜውና ፡ አለዐቅዱ ፡ ወደትጥቅ ፡ ትግል ፡ እንዲያመሩ ፡ አደረጓቸው ። ይህ ፡ በሀገር ፡ ዳር ፡ ድንበር ፡ የተዠመረ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ክንድ ፡ የኾነውን ፡ ሰራዊቷን ፡ የመውጋት ፡ ጐጂ ፡ ርምጃ ፥ አለውክልና ፡ ከመፈጸሙ ፡ ጋራ ፥ ከባድ ፡ የዐቅድም ፡ የስልትም ፡ ጥፋት ፡ ስለ ፡ ነበር ፥ አንድነቱን ፡ እጅጉን ፡ ጐዳው ።

ታሪክ ፡ ሰለ ፡ ኾነ ፥ ዛሬ ፡ ጥቂቱን ፡ ለምልክት ፡ ያኽል ፡ ልንናገረው ፡ እንችላለን ። ሊየተና ፡ ጄኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕዝብም ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሰራዊትም ፡ እጅግ ፡ የተወደዱና ፡ የተመሰገኑ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ መኰንን ፡ ነበሩ ። በተለይ ፡ ባርበኝነት ፡ ዘመን ፡ በወጣትነታቸው ፥ በሸዋ ፣ በጐዣም ፣ በወለጋ ፡ ተዘዋውረው ፡ በፈጸሟቸው ፡ ገድሎች ፤ ከድል ፡ በኋላም ፡ ዐዲስ ፡ አበባ ፡ ገብተው ፡ መላ ፡ ሀገሪቱን ፡ ሲያረጋጉ ፤ ቀጥሎ ፥ በሀገራዊው ፡ ዠግና ፡ በራስ ፡ አበበ ፡ አረጋይ ፡ መሪነት ፥ በጦር ፡ ሚኒስቴር ፡ ዋና ፡ ጸሓፊነታቸው ፡ ዘመናዊውን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ጦር ፡ ሰራዊት ፡ ሲያቋቁሙ ፤ ቀጥሎም ፡ በ*"ኤርትራ"* ፡ የኢትዮጵያ ፡ አገናኝ ፡ መኰንንነታቸው ፡ ወቅት ፥ በ*"ኢትዮጵያ ፡ ወይም ፡ ሞት"* ፡ የአንድነት ፡ ትግል ፡ ውስጥ ፥ ከባሕር ፡ ምድር ፡ ነዋሪ ፡ ዘንድ ፡ ያተረፉት ፡ ተወዳጅነት ፤ ከዚያም ፡ በሀገረ ፡ ገዢነት ፡ ባገለገሉባቸው ፡ በባሌ ፣ በኦጋዴን ፣ በጎንደር ፣ በሲዳሞ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛቶች ፤ በሕግ ፡ መወሰኛ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ አባልነት ፥ እንዲሁም ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ የመንግሥት ፡ ከፍተኛዎች ፡ ኀላፊነቶች ፡ ባበረከቱት ፡ የላቀ ፡ አገልግሎት ፤ ከመንግሥታዊ ፡ ኀላፊነት ፡ ሌላ ፥ በ*"ጥንታዊት ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሀገራዊ ፡ የዠግኖች ፡ ማኅበር"* ፡ ሊቀ ፡ መንበርነታቸውም ፡ ወቅት ፡ በቀሰቀሱት ፡ ሰፊ ፡ ሀገራዊ ፡ ንቅናቄ ፥ በእነዚህ ፡ ኹሉ ፡ ምክንያቶች ፡ ዝናቸውና ፡ ተሰሚነታቸው ፡ የገነነ ፡ ስለ ፡ ነበር ፥ ወደ ፡ ሀገር ፡ ቢዘልቁ ፡ የሚከተላቸው ፡ ሕዝብና ፡ ሰራዊት ፡ እጅግ ፡ አመዛኝ ፡ ይኾን ፡ ነበር ።

ታዲያ ፥ ጐንደው ፡ በመለየት ፡ ኢ.ዴ.ኅ.ን ፡ ካቋቋሙት ፡ አባላት ፡ መኻከል ፡ ብሪጋዲዬ ፡ ጄኔራል ፡ ነጋ ፡ ተገኝ ፡ የተባሉት ፡ መኰንን ፡ ይገኙበት ፡ ነበርና ፥ *"ጄኔራል ፡ ነጋ"* ፡ በሚለው ፡ የስም ፡ ሞክሼነት ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡ ሳይበላሽ ፡ አልቀረም ። ዐያሌ ፡ አገር ፡ አፍቃሪዎች ፡ ተነሣሥተው ፡ አለጊዜውና ፡ አለዐቅዱ ፡ በደርግ ፡ ላይ ፡ ሲሸፍቱ ፥ ተቀብሎ ፡ የሚያደራጃቸው ፡ ብቁ ፡ ድርጅታዊ ፡ አካል ፡ ባለመገኘቱ ፥ ተጋልጠው ፡ በቀላሉ ፡ ተደመሰሱ ። በዚህ ፡ በጠላት ፡ የውስጥ ፡ ዐወቅ ፡ ክፉ ፡ ደባ ፥ ትግሉ ፡ ትልቅ ፡ የድል ፡ ዐቅምና ፡ ዕድል ፡ መከነበት ። ጠላት ፡ የኢ.ዴ.ኅ.ን ፡ ተጋድሎ ፡ የፈለገው ፥ የኢትዮጵያን ፡ ሰራዊት ፡ በየአግጣጫው ፡ ወጥሮ ፡ ሊይዝበት ፣ ሊያባክንበትና ፡ ሊያደክምበት ፡ እንጂ ፥ *"ዴሞክራሲን"* ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሊያሰፍንበት ፡ አልነበረም ። ዛሬም ፡ ቢኾን ፥ ተመሳሳይ ፡ ሸር ፡ ይሠራብናል ።

***ሥ.መ.*** *፤ ብዙ ፡ ሳይቈይ ፡ የኢ.ዴ.ኅ. ፡ መሪዎች ፡ የውጊያውን ፡ ዐውድማ ፡ ትተው ፡ ወደምዕራቡ ፡ ዓለም ፡ ከተመለሱ ፡ በኋላ ፥ እቦታው ፡ ላይ ፡ የነበሩ ፡ ታጋዮች ፡ ጥሪያቸውን ፡ ለኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ አሰምተው ፡ ነበር ፤ የኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ መልስ ፡ ምን ፡ ኾነ ፨*

**ወ.ነ.** ፤ እውነት ፡ ነው ፤ *"የኢትዮጵያ ፡ ዴሞክራቲክ ፡ ታጋዮች"* ፡ በሚል ፡ ስያሜ ፡ ይንቀሳቀስ ፡ የነበረው ፡ የኢ.ዴ.ኅ. ፡ ሰራዊት ፥ ስመ ፡ ጥሩውን ፡ አገር ፡ አፍቃሪና ፡ የነጻነት ፡ ታጋይ ፡ አቶ ፡ መኰንን ፡ ተክለ ፡


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።

አረጋዊን ፡ በምክትል ፡ ሊቀ ፡ መንበርነት ፡ ከሠየመ ፡ በኋላ ፥ በኅዳር ፡ 21 ፡ ቀን ፡ 1972 ፡ ዓ.ም. ፡ ጉባኤው ፥ ከ 600 ፡ ያላነሱ ፡ የኢ..ዴ.ኅ. ፡ ታጋዮች ፡ በሱዳን ፡ በረሓ ፡ መክረውና ፡ ዘክረው ፥ ሊየተና ፡ ጬኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴን ፥ በሌሉበት ፥ ሊቀ ፡ መንበር ፡ ብለው ፡ በሙሉ ፡ ድምፅ ፡ መሾማቸውን ፡ በፊርማቸው ፡ አረጋግጠው ፥ የጥሪ ፡ ደብዳቤያቸውን ፡ ለንደን ፡ በስደት ፡ ለሚገኙት ፡ መሪያቸው ፡ ላኩ ። በተጓዳኝ ፥ ለሱዳን ፡ መንግሥትም ፡ ይህኑ ፡ በማብሠር ፥ ዐዲሱ ፡ ሊቀ ፡ መንበራቸው ፡ ወደ ፡ ሱዳን ፡ መምጣት ፡ እንዲፈቀድላቸው ፡ በጽሑፍ ፡ ጠየቁ ። ጬኔራሉ ፥ ጥሪውን ፡ ቢቀበሉም ፥ ርሳቸው ፡ የኢ..ሀ.ሥ.አ. ፡ እንጂ ፡ የኢ..ዴ.ኅ. ፡ አባል ፡ ስላልኾኑ ፥ ሹመቱን ፡ አልተቀበሉም ፤ ሰራዊቱን ፡ ግን ፡ ለኢ..ሀ.ሥ.አ. ፡ ዐላማ ፡ ለማሰለፍ ፡ ተስፋ ፡ ነበራቸው ።

ከብዙ ፡ ውጣ ፡ ውረድ ፡ በኋላ ፥ እሱዳን ፡ መግባት ፡ ተፈቅዶላቸው ፥ ሊየተና ፡ ጬኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ ኀርጡም ፡ ደርሰው ፡ ገና ፡ ጥቂቶቹን ፡ የታጋዩ ፡ ተወካዮች ፡ እንዳገኙ ፥ የሱዳን ፡ መንግሥት ፡ የጸጥታ ፡ ሚኒስትር ፥ አቶ ፡ ዑስመን ፡ ሰዒድ ፡ ራሳቸው ፡ እሊየተና ፡ ጬኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ ድረስ ፡ መጥተው ፥ *"ለጸጥታዎ ፡ ምንም ፡ ዋስትና ፡ ልንሰጥ ፡ አንችልምና ፥ በ24 ፡ ሰዓት ፡ ውስጥ ፡ ከሱዳን ፡ ብሔር ፡ እንዲወጡ"* ፡ የሚል ፡ ቀጪን ፡ ትዛዝ ፡ በማሰማታቸውና ፡ ይህው ፡ በመፈጸሙ ፥ ጉብኝታቸው ፡ ባጪሩ ፡ ተቋረጠ ። በታጋዩና ፡ ባመራር ፡ አካሉ ፡ ዘንድ ፡ ትልቅ ፡ ተስፋ ፡ መቍረጥ ፡ ደረሰ ።

***ሥ.መ.*** ፤ *ጬኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ ወደ ፡ ሱዳን ፡ ሲኼዱ ፡ ምን ፡ ዐቅደው ፡ ኖሯል ፧*

**ወ.ነ.** ፤ ለዚህ ፡ ጥያቄ ፡ የተሟላ ፡ መልስን ፡ ሊሰጡ ፡ የሚችሉ ፡ ርሳቸው ፡ ነበሩ ። ኾኖም ፥ ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ እንዳጫወቱኝ ፥ የኢትዮጵያን ፡ ሰራዊት ፡ በመውጋት ፡ ስለማይስማሙ ፥ በተገኘው ፡ ዐቅምና ፡ መንገድ ፡ ወደ ፡ መኻል ፡ አገር ፡ ዘልቆ ፥ ሕዝቡንና ፡ ሰራዊቱን ፡ ለኢ..ሀ.ሥ.አ. ፡ ዐላማ ፡ አስማምቶ ፡ በደርግ ፡ ላይ ፡ በማስነሣትና ፡ ሀገራዊ ፡ ሥልጣንን ፡ በማብጀት ፥ ያገሪቱን ፡ ስያሳዊ ፡ ችግር ፡ በሰላማዊ ፡ መንገድ ፡ መፍታት ፡ ይቻላል ፡ ብለው ፡ ያምኑ ፡ ነበር ። ከዚህ ፡ የባሰ ፡ አስቸጋሪ ፡ የኾነባቸው ፡ ግን ፡ የውጭ ፡ ኀይሎችን ፡ መሰናክል ፡ ማለፍና ፡ ተቃውሟቸውን ፡ ማሸነፍ ፡ ነበርና ፥ ያሳዝናል ፥ በዚህ ፡ ረገድ ፡ የተመኙት ፡ ሳይሳካ ፡ ቀረ ። ብዙ ፡ ሳይቈይ ፥ የኢ..ዴ.ኅ. ፡ ምክትል ፡ ሊቀ ፡ መንበር ፡ አቶ ፡ መኰንን ፡ ተክለ ፡ አረጋዊ ፡ እዚያው ፡ እሱዳን ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ በጠላት ፡ እጅ ፡ ሕይወታቸው ፡ ማለፉን ፡ በታላቅ ፡ ሐዘንና ፡ ቊጭት ፡ ሰማን ።

አቶ ፡ መኰንን ፡ ተክለ ፡ አረጋዊ ፡ ከስያሳ ፡ መሪነታቸው ፡ ጋራ ፥ የቀለም ፡ ታጋይ ፣ ታላቅ ፡ የሥነ ፡ ጽሑፍ ፡ ባለጸጋም ፡ ነበሩ ። በተለይ ፥ ሱዳን ፡ ኾነው ፡ ከደረሷቸው ፡ የግጥም ፡ ማስታወሻዎቻቸው ፡ ጥቂቶቹን ፡ ለማንበብ ፡ ታድዬ ፡ ነበር ፤ እጅግ ፡ የሚያስደንቅ ፡ ችሎታ ፡ ነበራቸው ። ድርሰቶቻቸው ፡ ኹሉ ፡ ከያሉበት ፡ ተሰብስበው ፡ በመጽሐፍ ፡ ታትመው ፡ ለሕዝብ ፡ ንባብ ፡ ሊበቁ ፡ ይገባል ።

***ሥ.መ.*** ፤ *ማን ፡ እንደ ፡ ገደላቸው ፡ ይታወቃልን ፧*

**ወ.ነ.** ፤ *"ዳኛ ፡ ሲገኝ ፡ ተናገር ፤ ውሃ ፡ ሲጠራ ፡ ተሻገረ"* ፡ ነው ፡ ተረቱ ፤ ባለንበት ፡ ኹኔታ ፡ ብዙ ፡ መናገሩ ፡ አይጠቅምም ። በዘመኑ ፥ መገደላቸውን ፡ ያረጋገጡ ፡ ታማኞች ፡ ሽማግሌዎችና ፡ ወገኖች ፡ ነበሩ ። የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ መንግሥቱን ፡ ሲያቆም ፥ ይህ ፡ የሀገራዊ ፡ ክዳት ፡ ወንጀል ፡ ትኽክለኛ ፡ ፍርዱን ፡ እንዲያገኝ ፡ ኢ..ሀ.ሥ.አ. ፡ ጉዳዩን ፡ ለፍትሑ ፡ ሥልጣን ፡ ማቅረቡ ፡ አይቀርም ።

***ሥ.መ.*** ፤ *የሱዳኑ ፡ መንገድ ፡ ተዘጋ ፡ ማለት ፡ ይቻላልን ፧*

***ወ.ነ.*** ፤ አዎን ፥ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ተዘጋ ። በወቅቱ ፡ ስለአፍሪቃ ፡ ዜና ፡ የሚጽፍ ፡ አንድ ፡ ምዕራባዊ ፡ መጽሔት ፦ *"ሱዳን ፥ ከቪዬትናም ፡ ጦርነት ፡ ወዲህ ፡ ትልቁ ፡ የሚባለውን ፡ የC.I.A. ፡ ወኪሎች ፡ ስብስብ ፡ የምታስተናግድ ፡ ሀገር ፡ ኾናለች"* ፡ ሲል ፡ እንደ ፡ ጠቈመው ፥ ያሜሪካ ፡ መንግሥት ፥ ከጥቂት ፡ የምዕራብና ፡ የዐረብ ፡ መንግሥታት ፡ ጋራ ፡ ኾኖ ፥ የሕ.ወ.ሐ.ት.ን[1] ፣ የ"ሻዕቢያ"ን[2] ፡ እና ፡ የኦ.ነ.ግ.ን[3] ፡ ጦርና ፡ ጠቅላላ ፡ ድርጅት ፡ በይፋ ፡ የሚያጠናክርበት ፡ የዘመቻ ፡ ዘመን ፡ ነበር ።

ቀደም ፡ ሲል ፥ ከታመኑ ፡ ምንጮች ፡ ለአንድነታችን ፡ በደረሰ ፡ የቃል ፡ መረጃ ፡ መሠረት ፥ በአሜሪካ ፡ መንግሥት ፡ *"ስቴይት ፡ ዲፓርትመንት"* ፡ ዋቢነት ፥ *"ሽካጎ ፡ ዩኒቨርስቲ"* ፡ በሠራው ፡ አጠቃላይ ፡ ስያሳዊ ፣ ጥርየታዊና ፡ ማኅበራዊ ፡ ጥናት ፥ *"«ዐማራዎችን» ፡ ከኢትዮጵያ ፡ የሥልጣን ፡ ሰገነት ፡ ለመቼውም ፡ ለማባረር ፥ ባንድ ፡ ወገን ፡ «ትግሬዎች»ን ፡ በሌላ ፡ ወገን ፡ «ኦሮሞዎች»ን ፡ አደራጅቶ ፡ በ«ዐማራዎች» ፡ ላይ ፡ ማስነሣት ፡ ይኖራል"* ፡ የሚለውን ፡ ድምዳሜውን ፡

---

1 ሕ.ወ.ሐ.ት. ፤ ሕዝባዊ ፡ ወያኔ ፡ ሐርነት ፡ ትግራይ ።
2 ሕ.ግ.ሐ.ኤ. ፤ ሕዝባዊ ፡ ግንባር ፡ ሐርነት ፡ ኤርትራ ።
3 ኦ.ነ.ግ. ፤ ኦሮሞ ፡ ነጻነት ፡ ግንባር ።


©ኢ..ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።

በዝርዝር ፡ ጥናቱ ፡ አቅርቦ ፡ ነበር ። የአሜሪካ ፡ "ስቴይት ፡ ዲፓርትመንት" ፡ በዚህ ፡ ረገድ ፡ ያለውን ፡ ስያስ ፡ (ወይም ፡ "ፖለሲይ") ፡ እና ፡ ዐቅድ ፡ በጥናቱ ፡ መሠረት ፡ ከላልሶ ፥ በወቅቱ ፡ ወደ ፡ አፈጻጸም ፡ መሸጋገሩ ፡ ይነገር ፡ ነበር ። ላፈጻጸሙ ፡ የሚረዱትን ፡ እንደ ፡ "ሻዕቢያ" ፣ ሕ.ወ.ሐ.ት. ፡ እና ፡ ኦ.ነ.ግ. ፡ ያሉትን ፡ የመጎንጠል ፡ ድርጅቶች ፡ አጠናከረ ፤ ሌሎችንም ፡ የ"ሕዝቦች"ን ፡ ፖለቲካ ፡ የሚሰብኩለትን ፡ እንደ ፡ E.P.D.A. ፡ ያሉትን ፥ ከC.I.A. ፡ በቀጥታ ፡ በሚከፈል ፡ ባጀትና ፡ ደመ ፡ ወዝ ፡ ለሥራ ፡ አሰማራ ።

***ሥ.መ.*** ፤ *ለዓለም ፡ የተለፈፈው ፡ ግን ፡ "ፀረ-ኮምዩኒስት" ፡ ዘመቻ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ነው ።*

**ወ.ነ.** ፤ እኛም ፡ ብንኾን ፥ መረጃው ፡ ከታመኑና ፡ በሥራውም ፡ ከተሰማሩ ፡ ሰዎች ፡ አንደበት ፡ ቀደም ፡ ሲል ፡ ባይደርሰን ፡ ኖሮ ፥ "ፀረ-ኮምዩኒስት" ፡ ዘመቻ ፡ ነው ፡ ብለን ፡ ምናልባት ፡ እንቀበል ፡ ነበር ። ዳሩ ፡ ግን ፥ ከኮምዩኒዝም ፡ ውድቀት ፡ ወዲህም ፡ ተጠናክሮ ፡ ቀጥሏል ። እስከ ፡ ዛሬ ፡ የተፈጸመውን ፡ መለስ ፡ ብለን ፡ ስንመለከት ፥ የተነገረን ፡ ዅሉ ፡ በትኽክል ፡ ተከናውኗል ፤ አኹንም ፡ ይከናወናል ።

«ትግሬዎች» ፡ ያሏቸውን ፡ ለማደራጀት ፥ እንግሊዞች ፡ በ1930ዎቹ ፡ የዠመሩትን ፡ የ"ቀዳማይ ፡ ወያኔ" ፡ ንቅናቄ ፥ ከ1960ዎቹ ፡ ወዲህ ፥ አሜሪካኖች ፡ ከእንግሊዞች ፡ ጋራ ፡ በመተባበር ፥ በሕ.ወ.ሐ.ት ፡ ስም ፡ "ዳግማይ ፡ ወያኔ"ን ፡ በሰፊው ፡ አደራጁት ፤ ዋና ፡ ጽሕፈት ፡ ቤቱም ፡ በደቡብ ፡ ለንደን ፡ ይገኝ ፡ ነበር ።

«ኦሮሞዎች» ፡ ያሏቸውን ፡ ደግሞ ፥ በባህላዊው ፡ የ"ገዳ" ፡ ሥርዐት ፡ ለማነሣሣት ፥ ሰፊ ፡ የኾነ ፡ የ"ፕሮፓጋንዳ" ፡ ዘመቻን ፡ አደራጁ ። በተለይ ፡ በጥቂት ፡ ያሜሪካና ፡ የምዕራብ ፡ አውሮፓ ፡ ዩኒቨርስቲዎች ፡ ሰባኪዎችን ፡ መደቡላቸው ። እነዚህም ፥ በእንግሊዝኛ ፡ ቋንቋ ፡ በሚታተሙ ፡ ጥናቶችና ፡ መጻሕፍት ፡ አማካይነት ፡ ስብከታቸውን ፡ አስፋፉ ። ሌሎቹንም ፡ የኅብረተሰብ ፡ ክፍሎች ፡ እንዲሁ ፡ በ«ዐማራዎች» ፡ ላይ ፡ ለማስነሣት ፥ ባህላዊ ፡ አሠራራቸውን ፡ በመከተል ፡ ሞካከሩ ።

***ሥ.መ.*** ፤ *የውጪ ፡ ኀይሎች ፡ በተለይ ፡ «ዐማራዎች» ፡ ላይ ፡ ለምን ፡ እንዲህ ፡ አነጣጠሩ ፡ ይላሉ ፧*

**ወ.ነ.** ፤ "ለምን ፧" ፡ ለሚለው ፡ ጥያቄ ፥ ሳንደርስባቸው ፡ የደረሱብን ፣ ሳንበድላቸው ፡ የበደሉን ፡ የውጪ ፡ ኀይሎች ፡ ራሳቸው ፡ ቢመልሱ ፡ ይሻል ፡ ነበር ። የኛ ፡ ድርሻ ፡ በመዠመሪያ ፡ ደረጃ ፡ መከላከል ፡ ሊኾን ፡ ይገባል ። ኾኖም ፥ ለጥያቄዎ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ መልሱን ፡ ልስጥ ። የኢትዮጵያ ፡ ብሔራዊ ፡ (ምድራዊ) ፡ አቀማመጥ ፡ እጅግ ፡ ዐቅዳዊ ፡ ነው ፤ ኢትዮጵያን ፡ ሳይቈጣጠሩ ፡ አፍሪቃንም ፡ ኾነ ፡ መካከለኛውን ፡ ምሥራቅ ፡ መቈጣጠር ፡ አይቻልም ። ባልሳሳት ፥ ሌኒን ፡ መሰለኝ ፦ አፍሪቃን ፡ የያዘ ፡ አውሮፓን ፡ ያዘ ፡ ያለው ። የቀደሙ ፡ የምልክዮሽ ፡ (ወይም ፡ የ"ኢምፖሪያሊዝም") ፡ ኀይሎች ፡ ዅሉ ፡ ምላጭ ፡ በሚያስውጥ ፡ እልክ ፡ ገሥግሠው ፡ እየመጡ ፥ እኢትዮጵያ ፡ ዳርቻዎች ፡ ሲደርሱ ፥ ዐማራ ፡ እሚሉት ፡ አለት ፡ ላይ ፡ እየተከሰከሱና ፡ ድል ፡ እየኾኑ ፡ ተመልሰዋል ።

ዛሬ ፥ የምልክዮሽ ፡ ኀይሎች ፡ አመጣጥ ፡ በዚሁ ፡ በምልክዮሽ ፡ መነሻነትና ፡ መድረሻነት ፡ እንጂ ፥ "ኦሮሞዎች"ና ፡ "ትግሬዎች" ፡ ላሏቸው ፡ የኅብረተሰብ ፡ ክፍሎች ፡ መብት ፡ ተቈርቍረው ፡ አይደለም ። ይህማ ፡ ቢኾን ፥ ላሜሪካ ፡ መደባይ ፡ ሕዝቦች ፣ ለጥቍሮች ፡ ዜጎቻቸውና ፡ ለቅኝ ፡ ግዛቶቻቸው ፡ መብት ፡ በቆሙ ፡ ነበር ። ባፍሪቃ ፡ ቀንድ ፡ ሊያቋቁሙት ፡ ያሰቡትን ፡ ባለቤት-አልቦ ፡ ውጥን-ቅጥ ፡ ተዳብሎ ፡ ወይም ፡ "ኮንፌደሬሽን" ፡ ሊያሰናክልባቸው ፡ የሚችለው ፡ አንድያ ፡ ኀይል ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ሀገራዊነት ፡ ወይም ፡ ዐማራነት ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ ርሱን ፡ ሊደመስሱ ፡ ተነሥተዋል ።

ይህ ፡ ጕዳይ ፡ ለዛሬው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ስያሳዊ ፡ ችግር ፡ ዋነኛው ፡ ምክንያት ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ ወደ ፡ ፊት ፡ በዝርዝር ፡ እንመለስበታለን ፤ ለጊዜው ፡ ግን ፥ ኹለት ፡ መሠረታውያን ፡ ነጥቦችን ፡ አመልክቼ ፥ በረገዱ ፡ የሚኖረኝን ፡ ገለጻ ፡ እገታለኹ ።

አንደኛ ፥ ባንዲት ፡ እግዝእት ፡ ሀገር ፡ የውስጥ ፡ ጕዳይ ፡ ሌላ ፡ መንግሥት ፡ ጣልቃ ፡ ሲገባ ፥ ይህ ፡ ከባድ ፡ ዋጋን ፡ የሚያስከፍል ፡ ጥፋት ፡ ነው ። ታሪክ ፡ በሚያሳዝን ፡ ኹኔታ ፡ ደጋግሞ ፡ አሳይቶናል ፤ ልቦናን ፡ ይስጣቸው ።

ኹለተኛ ፥ የኢትዮጵያን ፡ ሕዝብ ፡ "ሕዝቦች" ፡ ብሎ ፡ ለመከፋፈል ፡ መሞከር ፡ ፍጹም ፡ አላዋቂነት ፡ ነው ። ለጊዜው ፡ የያዘላቸው ፡ ይመስላቸው ፡ ይኾናል ፤ ነገር ፡ ግን ፡ አይዘልቁም ። ኢትዮጵያዊነት ፡ ወይም ፡ ዐማራነት ፡ ሀገራዊነት ፡ ነው ፤ በፈረንጆቹ ፡ አባባል ፡ "ሲቲዘንሺፕ" ፡ ነው ። ኢትዮጵያዊ ፡ ዅሉ ፡ "ዐም ፡ ሐራ ፡ - ፡ ነጻ ፡ ሕዝብ" ፡ ነው ፤ ሀገራዊ ፡ ነው ፤ ባለሀገር ፡ ነው ፤ አንድ ፡ ሀገራዊ ፡ ሕዝብ ፡ ነው ። "ሕዝብ" ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ ራሱ ፡ ውስጠ ፡ ብዙ ፡ ነው ፤ ውስጠ ፡ ብዙነት ፡ ሀብታችን ፣ መበልጸጊያችን ፣ መጐልበቻችን ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ እንወደዋለን ፡ እንጂ ፡ አንጠላውም ፤ ይበጀናል ፡ እንጂ ፡ አይጐዳንም ።


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።

ኢትዮጵያን ፡ ለማጥፋት ፡ የሚነሣ ፡ ኀይል ፥ ኹል ፡ ጊዜም ፡ ቢኾን ፥ የኢትዮጵያን ፡ ሕዝብ ፡ "የለም!" ፡ ብሎ ፡ በመካድ ፡ ይዠምራል ። ፋሺስቶች ፡ ሲወሩን ፡ ይህኑ ፡ ደንፍተውብን ፡ ነበር ። የዛሬውም ፡ የጎሳ ፡ "ናሽናሊዝም" ፡ ወይም ፡ "ውልደትዮሽ" ፡ የ"ፋሺዝም" ፡ የእንጀራ ፡ ልጅ ፡ ነውና ፥ "የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ የለም!" ፡ በማለት ፡ ዠምሯል ። የ"ኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፡ ሕገ ፡ መንግሥት" ፡ የኢትዮጵያ ፡ "ሕዝቦች" ፡ እንጂ ፥ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ የለም ፡ ብሎ ፡ በመካድ ፡ የስያሳ ፡ ጦርነቱን ፡ ዐውጆብናል ። ስለዚህ ፥ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ሊገዛለት ፡ አይገደድም ፤ ሊገዛለትም ፡ አይገባውም ። "እምቢ!" ፡ የማለት ፡ መሉ ፡ መብት ፡ አለለት ።

"ትግሬ" ፣ "ጐንደሬ" ፥ "ሱሪ" ፣ "ሐረሪ" ፥ "ወላይታ" ፣ "ከምባታ" ፥ ወዘተ. ፡ ቢባል ፡ ቅሉ ፥ ልዩነቱ ፡ የክፍለ ፡ ሀገር ፣ የቋንቋ ፣ የባህል ፣ የውልደት ፡ እንጂ ፡ የሀገራዊነት ፡ አይደለም ። የጎሳ ፡ ማንነት ፡ በኢትዮጵያዊ ፡ ሀገራዊነት ፡ ወይም ፡ በዐማራነት ፡ ከተሻረ ፡ 3000 ፡ ዘመን ፡ ዐልፏል ። ነገሩን ፡ በ"ዘር" ፡ በውልደት ፡ ሐረግ ፡ እንየው ፡ ብንልም ፡ እንኳ ፥ አብዛኛው ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ከኹለት ፣ ከሦስት ፡ ውልደቶች ፡ ወይም ፡ ጎሳዎች ፡ ይወለዳል ፤ በእናትም ፡ በአባትም ፡ካንድ ፡ ውልደት ፡ ብቻ ፡ የሚወለድ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ምናልባት ፡ ከጠቅላላው ፡ ሕዝብ ፡ 2% ፣ ግፋ ፡ ቢል ፡ 5% ፡ ቢኾን ፡ ነው ። ዛሬ ፡ እፊት ፡ እፊት ፡ የሚሉት ፡ የ"ጎሳ ፡ ድርጅት" ፡ መሪዎች ፡ -- ፡ በጠቅላላ ፡ ማለት ፡ ይቻላል ፡ -- ፡ በሚመኩበት ፡ የ"ዘር" ፡ ሐረግ ፡ መዘዛ ፡ ሲፈተሹ ፥ በከፊል ፡ እንጂ ፡ በሙሉ ፡ አንዳቸውም ፡ እንኳ ፡ ካንድ ፡ ጎሳ ፡ ብቻ ፡ አይወለዱም ።

በእውነቱ ፥ በኢትዮጵያ ፡ ላይ ፡ የተፈጸመው ፡ ደባ ፡ ከደባ ፡ ኹሉ ፡ የከፋ ፥ ሰብኣዊ ፡ ኅሊና ፡ ያነቃዋል ፡ ተብሎ ፡ የማይገመት ፡ ፍጹም ፡ ዲያብሎሳዊ ፡ ክፋትና ፡ ጭካኔ ፡ ነው ። ሰላማዊውን ፣ ሥርዐት ፡ አክባሪውን ፣ ሥልጡኑን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፥ "አንተ ፡ በኦሮሞነትኽ ፡ ተበድለኻል ፤ ... ፡ አንተ ፡ በትግሬነትኽ ፡ ተበድለኻል ፤ ... ፡ አንተ ፡ በሶማሌነትኽ ፡ ተበድለኻል ፤ ... ፡ አንተ ፡ በኤርትራዊነትኽ ፡ ተበድለኻል ፤ ... ፡ ወዘተ." ፡ እያሉ ፡ መስበክ ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፥ ወንድሙንና ፡ እኅቱን ፡ የሚገድልበትን ፡ መሣሪያ ፡ በማስታጠቅ ፣ ስልት ፡ በማመልከትና ፡ የውሸቸ ፡ ወሬን ፡ በመንዛት ፥ ኀምሳ ፡ ዓመት ፡ ሙሉ ፡ በጽናት ፡ ማጨፋጨፍ ፥ ከእግዚአብሔር ፡ ካልኾነ ፡ በቀር ፥ ከሰው ፡ ልጅ ፡ ፍርድ ፡ በፍጹም ፡ አይገኝለትም ።

እግዚአብሔር ፡ ፍርድን ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ይስጠው ።

የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ፈጽሞ ፡ የተዋሐደ ፥ የማንንም ፡ የማይመኝ ፣ በራሱ ፡ ዐዳሪ ፣ ሥልጡን ፡ ሕዝብ ፡ ነው ። "ልዩ ፡ ልዩ ፡ ማንነቶች ፡ አሉን" ፡ ማለት ፡ "በመንግሥት ፡ ውስጥ ፡ መንግሥቶች ፡ ይቋቋሙልን" ፡ ማለት ፡ አይደለም ። ከማንም ፡ በፊት ፥ በሀገራዊነት ፡ አንድ ፣ የማይከፋፈል ፣ ኢትዮጵያዊ ፡ ነጻ ፡ ሕዝብ ፡ ኾነናል ፤ አንድያ ፡ ሀገራዊ ፡ ቋንቋችን ፡ ዐማርኛ ፡ ወይም ፡ "ነጻ ፡ ሕዝብኛ" ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ "ሀገርኛ" ፡ ነው ፤ ሀገራችንም ፡ አንዲት ፡ ኢትዮጵያ ፡ ናት ። ማንነቶቻችንን ፣ ባህሎቻችንን ፡ በ"ክልል" ፡ ሳይኾን ፡ በመላ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ማበልጸግና ፡ ማዋሐድ ፡ ከማንም ፡ የማንቸራቸው ፡ ሀገራውያን ፡ መብቶቻችን ፡ ናቸው ።

በዓለም ፡ ታሪክ ፡ ሀገራዊነትን ፡ ያሸነፈው ፡ ኀይል ፡ አልታየም ፤ ወደ ፡ ፊትም ፡ አይታይም ። ዓለም ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ይነኰራል ፥ ያዘግማል ። ሀገራዊነት ፡ በርትዕ ፡ ሥልጣኔ ፡ የሚገኝ ፡ ኹነት ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ ባሕርያዊ ፡ ነው ፤ ርሱን ፡ አጠፋለኹ ፡ ብሎ ፡ መነሣት ፥ እነመንግሥቱ ፡ ኀይለ ፡ ማርያም ፦ "ተፈጥሮን ፡ ከቍጥጥራችን ፡ ሥር ፡ እናውላታለን!" ፡ ብለው ፡ ከዘበቱበት ፡ ያልተሻለ ፡ ዘበት ፡ ነው ። ለዘለቄታው ፡ ኢትዮጵያ ፡ አትሠጋም ።

**ሥ.መ.** ፤ ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ ጊዜያዊ ፡ ፈጻሚ ፡ ምክሩን ፡ በሚያዝያ ፡ ወር ፡ 1982 ፡ ዓ.ም. ፡ ሠይሟል ፤ ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ ጕዞው ፡ እንዴት ፡ ነበር ፧

**ወ.ነ.** ፤ ሥራው ፡ ግዴታችን ፡ የኾነውን ፡ ያኽል ፡ በራሱ ፡ ታላቅ ፡ ደስታንም ፡ ይሰጣል ፤ ከውጭ ፡ ሀገር ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ደግሞ ፥ የተለየ ፡ ጊድርም ፡ አስቸጋሪነትም ፡ አለው ።

በመዠመሪያ ፡ ደረጃ ፥ ስደተኛው ፡ ለሰላማዊ ፡ ሰልፍ ፡ እስከ ፡ መውጣት ፥ ወይ ፡ ጉባኤ ፡ ሲጠራ ፡ እስከ ፡ መገኘት ፡ እንጂ ፥ ቿክ ፡ ብሎ ፡ የድርጀታ ፡ ሥራን ፡ አለዋጋ ፡ (ማለት ፥ በነጻ) ፡ ለመሥራት ፡ ብዙ ፡ ፈቃደኛ ፡ አልነበረም ። ፈቃደኞች ፡ ቢኖሩም ፥ በቦታ ፡ ሩቅ ፡ ለሩቅ ፡ በመገኘታቸው ፡ ምክንያት ፥ ዐብሮ ፡ ለመሥራት ፡ እጅግ ፡ ፈተና ፡ ነበር ፤ የመገናኛው ፡ ዐቅምም ፡ እንደ ፡ ዛሬው ፡ ምቹና ፡ ወጪን ፡ ቈጣቢ ፡ አልነበረም ።

ስደተኛው ፡ ይበልጡን ፡ ኑሮን ፡ ለማሸነፍ ፡ ይሯሯጣል ፤ ይህም ፡ ያስመሰግነዋል ። ሥራው ፡ ኹሉ ፡ የተሠራው ፥ ስደተኛው ፡ በለገሰን ፡ ዐቅምና ፡ ድጋፍ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ ልባዊ ፡ ምስጋናችንን ፡ እናቀርብለታለን ።

በማወራኛ ፡ (በ"ሜዲያ") ፡ ረገድ ፥ የዛሬ ፡ 25 ፡ ዓመት ፡ "ኢንተርኔት" ፡ አልነበረም ፤ ማንኛውንም ፡ ዜናና ፡ መግለጫ ፡ በመላው ፡ ዓለም ፡ የምናወራኘው ፡


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።

በበራሪ ፡ ወረቀትና ፡ በ"*ሥልጡንሕዝብና*" ፡ መዜንው ፥ በከባድ ፡ ወጪ ፡ ነበር ። ከ"*ነጻው ፡ ፕሬስ*"ም ፡ የሚያስተጋባልን ፡ የማስተውሰው ፡ አንድም ፡ አልነበረ ። እውነቱን ፡ ለመናገር ፥ ከኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ መግለጫዎች ፡ መኻከል ፥ አንድ ፡ መግለጫ ፡ ብቻ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከሚታተሙ ፡ መጽሔቶች ፡ ባንደኛው ፡ ተጠቅሶ ፡ አይቻለኹ ። ርሱም ፡ በክፍለ ፡ ሀገር ፡ ኤርትራ ፡ የተደረገውን ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ ሕዝባዊ ፡ ፈረዳ ፡ ("*ሬፌራንደም*") ፡ በመቃወም ፡ ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ ያወጣው ፡ የውሳኔ ፡ መግለጫ ፡ ነበር ። በወቅቱ ፥ "*ጦቢያ*" ፡ የተባለው ፡ መጽሔት ፡ ላንባቢዎቹ ፡ እንዷለ ፡ ሲያወጣው ፥ መጠኑ ፡ A4 ፡ (ሙሉ ፡ ገጽ) ፡ የነበረውን ፡ መግለጫ ፡ በA6 ፡ (ሩብ ፡ ገጽ!) ፡ መጠን ፡ አዶግዱጎ ፡ ዐትሞት ፥ በማጕሊያ ፡ ካልኾነ ፡ በቀር ፡ ፈጽሞ ፡ የማይነበብ ፡ እንደ ፡ ነበር ፡ አስታውሳለኹ ።

ዛሬ ፥ "*ኢንተርኔት*" ፡ ይህን ፡ ችግር ፡ በመጠኑ ፡ ያስወግድልናል ፡ ብለን ፡ ነበር ፤ መቼ ፡ እንዲህ ፡ ቀላል ፡ ... ። ዝርዝር ፡ ነገሩን ፡ ትተን ፥ ካሥር ፡ ዓመት ፡ ወዲህ ፥ በስደት ፡ ባለንባት ፡ ብሪታንያ ፡ የአንድነታችን ፡ የባንክ ፡ ሒሳብ ፡ አላግባብ ፡ ተዘግቶብናል ፤ እንዲሁም ፡ የፖስታ ፡ ሣጥናችን ፡ ከዓለም ፡ ዐቀፍ ፡ ስምምነቶች ፡ ውጪ ፡ ተመዝብሮብን ፡ ልንዘጋው ፡ ተገደናል ። ከኹሉ ፡ የባሰ ፥ ከአባላታችን ፡ ውስጥ ፡ ዋነኞቹ ፡ የምንላቸው ፡ ከ25 ፡ ዓመት ፡ ላላነሰ ፡ ሠርቶ ፡ ከመብላት ፡ በተዘዋዋሪ ፡ ታግደውብናል ።

የባንክ ፡ ሒሳቡም ፡ ይቅርብን ፥ የፖስታ ፡ ሣጥኑም ፡ ይቅርብን ፤ አኹን ፡ ደግሞ ፡ ከብሪታንያ ፡ በኢንተርኔቱ ፡ እንሠራለን ፡ ስንል ፤ ርሱም ፡ መሥመሩ ፡ እየተጠለፈና ፡ እየተቈራረጠ ፡ ሥራን ፡ አላሠራ ፡ ብሎናል ። በብሪታንያ ፡ ውስጥ ፡ የደረሰብንን ፡ በማገናዘብ ፥ ቀደም ፡ ሲል ፥ የኢ.ሀ.ሥ.አ.ን ፡ መርበቢያ ፡ ("ዌብ ፡ ሳይት") ፡ ፈረንሳይ ፡ አገር ፥ የእጦማር ፡ መገኛን ፡ ደግሞ ፡ ጀርመን ፡ አገር ፡ አድርገናቸው ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፥ የኢንተርኔት ፡ መሥመራችን ፡ መቈራረጥ ፡ አልበቃ ፡ ብሎ ፥ በፍራንስም ፡ በጀርመንም ፡ ያሉት ፡ ኹለቱም ፡ መርበቢያዎቻችን ፡ ከወር ፡ በፊት ፡ ታግደውብን ፥ ለማስለቀቅ ፡ አኹን ፡ ድረስ ፡ እንጨቃጨቃለን ።

ከማይጠበቀው ፡ አግጣጫ ፡ ይህ ፡ ዐልፎ ፡ ዐልፎ ፡ የሚፈጸምብንን ፡ ብቀታና ፡ ፍትራ ፥ በስደተኛ ፡ ይሉኝታ ፥ "*ሆድ ፡ ይፍጀው*" ፡ ብለን ፡ ችለነው ፡ ኖረናል ፤ አኹን ፡ ግን ፡ ፈጽሞ ፡ ሥራችንን ፡ መሥራት ፡ እማንችልበት ፡ ደረጃ ፡ ላይ ፡ ደረስን ። ከንግዲህ ፡ ኹኔታችንን ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፣ ለተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ የሰብአውያን ፡ መብቶች ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፣ ለሚመለከታቸው ፡ መንግሥታት ፣ ለሰብአዊ ፡ መብት ፡ ተሟጋቾች ፡ ተቋማት ፣ ለማወራኛ ፡ ድርጅቶችና ፡ ለመላው ፡ የዓለም ፡ ኅብረተሰብ ፡ ስሜት ፡ ለማድረስ ፡ ወስነናል ።

የኾነው ፡ ኾኖ ፥ እግዚአብሔር ፡ ይመስገን ፥ በዚህ ፡ ኹሉ ፡ ዘመን ፡ አገር ፡ ቤት ፡ ብንኾን ፡ ይደርስብን ፡ የነበረው ፡ የከፋ ፡ አደጋ ፡ አልደረሰብንም ።

***ሥ.መ.*** ፤ *ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ ከውጭ ፡ መንግሥታት ፡ የጠየቀውስ ፡ ድጋፍ ፡ ኖሯልን ፧*

**ወ.ነ.** ፤ በ1970ዎቹ ፥ በምዕራቡ ፡ ዓለም ፥ "*የዴሞክራሲ ፡ አረማማጆች*" ፡ ከተባሉ ፡ መንግሥታት ፡ ውስጥ ፡ እጥቂቶቹ ፡ ዘንድ ፡ ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ ድጋፍን ፡ ጠይቆ ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ሙከራው ፡ ኹሉ ፡ ከሽፏል ። በተለይ ፡ ካንደኛው ፥ በተዘዋዋሪ ፡ የመጣለት ፡ መልስ ፡ የዛቻ ፡ ነበር! ፡ እጥቂት ፡ የአፍሪቃና ፡ የእስያ ፡ መንግሥታትም ፡ ዘንድ ፡ ርዳታን ፡ ጠይቆ ፥ ይህም ፡ ፍሬቢስ ፡ ኾኖ ፡ ቀርቷል ።

ሚያዝያ ፡ 13 ፡ ቀን ፡ 1982 ፡ ዓ.ም. ፡ ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ ዘጠኝ ፡ አባላት ፡ ያሉትን ፡ "*ጊዜያዊ ፡ ፈጻሚ ፡ ምክር*" ፡ በወግ ፡ ሠይሞ ፥ ሥራውን ፡ አጠናክሮ ፡ ቀጠለ ። ሊየተና ፡ ገኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ የምክሩ ፡ ሊቀ ፡ መንበር ፡ ኾኑ ፤ እኔም ፡ ከዚሁ ፡ ዕለት ፡ አንሥቶ ፡ የምክሩ ፡ አባል ፡ ኾኛለኹ ።

"*ሥልጡንሕዝብና*" ፡ መዜንውም ፡ መስከረም ፡ 1 ፡ ቀን ፡ 1983 ፡ ዓ.ም. ፡ የመዠመሪያ ፡ ዕትሙን ፡ በነጻ ፡ አሠራጨ ።

ጉባኤዎችን ፡ በምዕራብ ፡ አውሮፓና ፡ በሰሜን ፡ አሜሪካ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ከተማዎች ፡ አካኺደናል ፤ እየተጋበዝንም ፡ ተሳትፈናል ። በኹሉም ፡ ቦታዎች ፡ የሕዝቡ ፡ አቀባበል ፡ በጣም ፡ ተስፋ ፡ ሰጥቶን ፡ ነበር ። በመኻከሉ ፥ በግንቦት ፡ ወር ፡ 1983 ፡ ዓ.ም. ፥ የለንደኑ ፡ የዕርቅ ፡ ጉባኤ ፡ ተጨናግፎ ፥ "*የሽግግር ፡ መንግሥት*" ፡ የተባለው ፡ አላግባብ ፡ ተቋቋመ ። የኢትዮጵያ ፡ ኹኔታ ፡ ከድጡ ፡ ወደ ፡ ማጡ ፡ ገባ ። ደርግ ፡ በሀገሪቱ ፡ የዋለው ፡ በደልና ፡ ጥፋት ፡ እጅግ ፡ ከባድ ፡ ስለ ፡ ነበር ፥ ሕዝቡ ፡ የመከላከል ፡ ዐቅሙን ፡ ፈጽሞ ፡ ዐጥቶ ፡ ኖሮ ፥ ያሳዝናል ፥ መመከት ፡ ተሳነው ።

ይህ ፥ አኹን ፡ ታሪክ ፡ ኾኗል ፤ የኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ ትግል ፡ እዚህ ፡ ደርሷል ። ዛሬም ፥ ተመሳሳይ ፡ አደጋ ፡ እንዳለብን ፡ እናውቃለን ። ዛሬም ፡ እንደ ፡ ጥንቱ ፡


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።

በሥልጡንሕዝብና ፡ ርትዕ ፡ ጸንተን ፡ እስከ ፡ ታገልን ፡ ድረስ ፥ አንድነታችን ፡ ዐላማውን ፡ እንደሚፈጽም ፡ አንጠራጠርም ።

*ሥ.መ.* ፤ *ወደዛሬው ፡ የንግግራችን ፡ ርእስ ፡ እናምራና ፥ ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ መሠረታዊ ፡ ደንቡን ፡ ለምን ፡ አሻሻለ ፧ የማሻሻያዎቹስ ፡ ይዘት ፡ ምንድን ፡ ነው ፧*

**ወ.ነ.** ፤ ቀደም ፡ ሲል ፡ እንደ ፡ ገለጥኹት ፥ ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ የተመሠረተው ፡ በ 1967 ፡ ዓ.ም. ፡ ነው ፤ መሠረታዊ ፡ ሰነዱም ፡ ከሞላ ፡ ጐደል ፡ የ 1967 ፡ ዓ.ም. ፡ ነው ። በ 1983 ፡ ዓ.ም. ፡ መጠነኛ ፡ ማሻሻያ ፡ ቢደረግለትም ፥ ሰነዱ ፡ በመሠረቱ ፡ ያነጣጠረው ፡ በደርግ ፡ የውንብድና ፡ ይዘት ፡ አንጻር ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ የተከታተሉትን ፡ ያገዛዝ ፡ ለውጦች ፥ ወደ ፡ ፊትም ፡ ሊለጥቁ ፡ የሚችሉትን ፡ አጠቃሎ ፡ በሚያስተናግድ ፡ መልክ ፡ አኹን ፡ ልናድሰው ፡ ወስነናል ። በስልት ፡ ረገድ ፡ እንጂ ፥ በዐላማ ፡ ረገድ ፡ የተለወጠ ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ የለም ፤ ወደ ፡ ፊትም ፡ አይኖርም ።

ለአባሎቻችንና ፡ ለደጋፊዎቻችን ፥ እንዲሁም ፡ ለመላው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ቀዳሚ ፡ ንባብና ፡ ትችት ፡ እንሆ ፡ በረቂቅነት ፡ አቅርበነዋል ። ሰነዱን ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ከመርበቢያችን ፡ ከ ፦

www.slttunhzb.net

ሊያገኘው ፡ ይችላል ። የሕዝብን ፡ አስተያየት ፡ ተቀብለን ፥ ረቂቁን ፡ በርሱ ፡ መሠረት ፡ አሻሽለን ፥ በጉባኤ ፡ ከጸደቀ ፡ በኋላ ፥ ለሚገጥመን ፡ ተለዋዋጭ ፡ ስያሳዊ ፡ ኹኔታ ፡ ኹሉ ፡ የሚመጥነውን ፡ የትግል ፡ ስልት ፡ እንቀርጽበታለን ።

የማሻሻያዎቹ ፡ ዋነኛ ፡ ግብ ፥ ደንቡን ፡ አጠቃላይ ፡ ማድረግ ፡ ነው ። የደርግ ፡ ይዘት ፡ እንዳለፈና ፡ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፡ ይዘት ፡ እንደ ፡ ተተካ ፡ ኹሉ ፥ ነገ ፡ ደግሞ ፥ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፡ ይዘት ፡ ዐልፎ ፡ በሌላ ፡ በ"ሣልሳዊ ፡ ደርግ" ፡ ይዘት ፡ ቢተካም ፡ እንኳ ፥ ይህ ፡ አኹን ፡ የሚሻሻለው ፡ መሠረታዊ ፡ ሰነዳችን ፡ ብቁ ፡ ኾኖ ፡ ያዘልቀናል ። "ሣልሳዊ ፡ ደርግ" ፡ እንዳይተካብን ፡ ግን ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ጋራ ፡ የተቻለንን ፡ ኹሉ ፡ እናደርጋለን ፤ እግዚአብሔርም ፡ ይረዳናል ።

*ሥ.መ.* ፤ *እስከ ፡ ስንት ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ይጸድቃል ፡ ብለው ፡ ይገምታሉ ፧*

**ወ.ነ.** ፤ እላይ ፡ ጠቀስ ፡ ያደረግኹልዎ ፡ የመገናኛ ፡ ችግሮች ፡ እጅጉን ፡ አዘግይተውናል ። ጉዳዩን ፡ ገና ፡ በጥር ፡ ወር ፡ 2011 ፡ ዓ.ም. ፡ ይፋ ፡ ለማድረግ ፡ ተነሥተን ፡ ነበር ፤ ዋና ፡ የመገናኛ ፡ መሣሪያችን ፡ የኾነው ፡ የኢትነርኔት ፡ አገልግሎታችን ፡ እየተቈራረጠ ፡ የወራት ፡ ጊዜ ፡ ጠፍቶብን ፡ እስካኹን ፡ ዘግይተናል ። አኹን ፡ እንደ ፡ ምንም ፡ ይፋ ፡ አውጥተነዋል ፤ ከንግዲህ ፡ ከአባላትና ፡ ከደጋፊዎቻችን ፡ እንዲሁም ፡ ከኢትዮጵያውያን ፡ ኹሉ ፡ የሚደርሱንን ፡ አስተያየቶች ፡ እያገናዘብን ፥ ማሻሻያዎቹን ፡ ወስነን ፡ እንዳዋሐድናቸው ፥ የታደሰውን ፡ መሠረታዊ ፡ ሰነድ ፡ ይፋ ፡ እናወጣለን ፤ እስከ ፡ ሠኔ ፡ ወር ፡ 2011 ፡ ዓ.ም. ፡ መጨረሻ ፡ ለማጽደቅ ፡ ዐቅደናል ።

አስተያየታቸውን ፡ በጽሑፍ ፡ ሊያደርሱልን ፡ ለሚሹ ፡ ኹሉ ፥ በዚሁ ፡ አጋጣሚ ፥ ዐዲሱን ፡ የኢ-ጦማር ፡ አድራሻችን ፡ እንደሚከተለው ፡ እናመለክታለን ፦

sh1@ttomar.net

በስልክ ፡ ሊያገኙን ፡ የሚሹ ፡ ደግሞ ፥ ባንከርት ፡ ስልካችን ፦

(ለንደን) 00 44 7496541590

ሊደውሉልን ፡ ይችላሉ ።

*ሥ.መ.* ፤ *ይህ ፡ የማሻሻል ፡ ሥራ ፡ በወቅቱ ፡ በሀገራችን ፡ ከተከሠተው ፡ የለውጥ ፡ አዝማሚያ ፡ ጋራ ፡ ግንኙነት ፡ ያለው ፡ ይመስላል ።*

**ወ.ነ.** ፤ ርግጥ ፡ ነው ፥ ቢያንስ ፡ በኹለት ፡ ረገድ ፡ ግንኙነት ፡ አለው ። ለውጥ ፡ ስለ ፡ መምጣቱ ፡ ማንም ፡ የሚጠራጠር ፡ አልነበረም ፤ ሥርዐቱ ፡ መፍገምገም ፡ ከዠመረ ፡ ቈይቷል ። ለውጡም ፡ ገና ፡ "ሀ" ፡ ተባለ ፡ እንጂ ፥ አላለቀም ። "ሊቀለበስ ፡ ይችላል" ፡ ብለው ፡ የሚሠጉም ፡ አሉ ፤ ቢቀለበስም ፡ ቅሉ ፥ ውጤቱ ፡ ፍርሰታቸውን ፡ ከማፋጠን ፡ ሌላ ፡ ለቀልባሾቹ ፡ የሚያመጣላቸው ፡ ጥቅም ፡ አይኖርም ። ይህ ፡ የለውጥ ፡ ዥማሬ ፡ ወደ ፡ ደግ ፡ አግጣጫ ፡ ሊመራን ፡ የሚችለውን ፡ ያኽል ፥ ካልተጠነቀቅንና ፡ ተፈላጊውን ፡ ሥራና ፡ መሥዋዕትነት ፡ በማስተዋልና ፡ በወቅቱ ፡ ካልፈጸምንለት ፥ አኹንም ፡ ቢኾን ፥ የሥርዐት ፡ መደርመስንና ፡ የሕዝብን ፡ መጐዳት ፡ ሊያስከትልብን ፡ ይችላል ። ይህን ፡ በማሰብ ፥ በተቻለን ፡ ፍጥነት ፡ ለመላ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ድምፃችንን ፡ ለማሰማት ፡ ወስነናል ።

ኹለተኛ ፡ ደግሞ ፥ ሀገር ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ ከሕዝባችን ፡ ጋራ ፡ በአንድነት ፡ ሰላማዊ ፡ ትግሉን ፡ የመቀጠሉ ፡ ዕድል ፡ ከመቼውም ፡ የበለጠ ፡ ተገኝቷል ። ይህም ፡ የበኩሉን ፡ ዝግጅት ፡ ይጠይቃል ። አንዱ ፡ የደንቡ ፡ መሻሻል ፡ ነው ፥ ሌሎችም ፡ ተጓዳኞች ፡ ሥራዎች ፡ አሉ ፤


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።

በቅርብ ፡ ይጠናቀቃሉ ።

ለዚህ ፡ ደኀኛ ፡ ውጤት ፡ የበቃነው ፥ ሀገር ፡ አፍቃሪዎች ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ነጻነት ፣ ለሥልጡንሕዝብና ፡ እና ፡ ለሕዝቧ ፡ እግዚእና ፡ መከበር ፡ ብለው ፡ ውድ ፡ ሕይወታቸውን ፡ ስለ ፡ ሠዉልን ፡ ነውና ፥ ምስጋናችን ፡ በሐዘናችን ፡ ልክ ፥ ፍጹም ፡ ነው ፤ አክብሮታችንም ፡ ታላቅ ፡ ነው ።

የሞቱትን ፡ ሰማዕታት ፡ ነፍስ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይማርልን ፤ ወገኖቻቸውንም ፡ ያጽናናልን ። ባካልም ፡ በመንፈስም ፡ የተጐዱትን ፡ ወገኖቻችን ፡ ኹሉ ፡ ይጠግንልን ። መሥዋዕታቸው ፡ ከንቱ ፡ አልኾነም ፤ ሀገርንና ፡ ነጻነትን ፡ ዋጅቷል ። እኛም ፥ የያዝነውን ፡ የሥልጡንሕዝብና ፡ ዐላማ ፡ እዳር ፡ ሳናደርስ ፡ አናርፍ ፣ አንመለስም ።

*ሥ.መ.* ፤ *ለውጡ ፡ ምኑ ፡ ላይ ፡ ነው ፡ ይላሉ ፧*

**ወ.ነ.** ፤ ከንግግር ፡ በላይ ፥ በገቢር ፡ የተፈጸመ ፡ የእስረኞች ፡ መፈታትና ፥ የተቀናቃኞች ፡ ድርጅቶች ፡ ወደ ፡ ሀገር ፡ መመለስ ፥ በሰላምም ፡ ዐላማቸውን ፡ ከሞላ ፡ ጐደል ፡ ማስተዋወቅ ፡ መቻላቸው ፡ የነበረውን ፡ ኹኔታ ፡ በመጠኑ ፡ ለውጦታል ፤ ዐሌ ፡ አይባልም ። ያንኑ ፡ ያኽል ፡ ግን ፥ ገና ፡ ያልተፈቱትና ፡ የጠፉት ፡ ወገኖቻችን ፡ ጉዳይ ፡ ያሳስበናል ፤ እነዚህ ፡ ኹሉ ፡ ባስቸኳይ ፡ እንዲፈቱም ፣ እንዲገኙም ፡ ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ ይጠይቃል ። በተለይ ፡ በክፍለ ፡ ሀገር ፡ ትግራይ ፡ ስውሮች ፡ እስር ፡ ቤቶች ፡ ውስጥ ፡ የታጐሩትን ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ የመብት ፡ ታጋዮች ፥ በስሙ ፡ የሚነገድበት ፡ የክፍለ ፡ ሀገሩ ፡ ኗሪ ፡ ራሱ ፡ እንዲያስፈታቸው ፡ ጥሪያችንን ፡ እናስተላልፍለታለን ።

ኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ. ፡ ምርጫ ፡ አልነበረውም ፤ ለውጥ ፡ በግድ ፡ መጥቶበታል ። ግድን ፡ እምቢ ፡ ብሎ ፡ የት ፡ ይደርሷል ፧ ከሥልጣኑ ፡ ሰገነት ፡ በሰላም ፡ እንዲወርድ ፡ ኹላችንም ፡ ልንረዳው ፡ ይገባል ። አለዚያ ፥ አኹንም ፡ ቦታውን ፡ ለብቻው ፡ ብንለቅለት ፥ የሚመረኰዘው ፡ ምርኵዝ ፣ የሚደገፈው ፡ ደገፍ ፡ ዐጥቶ ፡ መደርመሱ ፡ የማይቀር ፡ ዕጣው ፡ ይኾናል ። የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፡ ይዘት ፡ ወይም ፡ "ሬዢም" ፥ በመሬት ፡ መንቀጥቀጥ ፡ እንደ ፡ ተናጋ ፡ ሕንጻ ፥ ከላይ ፡ እስከ ፡ ታች ፡ ተሠነጣጥቋል ። ብንተወው ፡ በገዛ ፡ እጁ ፡ ይፈርሳል ፤ ዐብረውም ፡ ብዙ ፡ ወገኖቻችን ፡ ይጐዳሉ ። ይህን ፡ ለመናገር ፡ ነቢይ ፡ መኾን ፡ አያሻም ፤ በጕልሕ ፡ የሚታይ ፡ እውን ፡ ነው ። የአሜሪካ ፡ መንግሥት ፥ በቀል ፡ በሚመስል ፡ አደራረግ ፥ ደቡብ ፡ አፍሪቃ ፡ የተፋቸውን ፡ የ"አፓርትሀይድ ፡ ሥርዐት" ፡ በእጀ ፡ መናኛ ፡ ሲጭንብን ፥ አኹን ፡ ለምናየው ፡ ፍርሰት ፡ ምክንያት ፡ ኾኗል ። ማንኛውም ፡ አካል ፡ ባዕድ ፡ ነገር ፡ ሲገባበት ፡ የመበላሸት ፡ ጠባይ ፡ አለው ፤ ይህ ፡ ባዕድ ፡ ነገር ፡ በግድ ፡ ቢጸናበት ፡ ደግሞ ፥ አካሉን ፡ ፈጽሞ ፡ አማስኖና ፡ መርዞ ፡ ይገድለዋል ። በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፡ ይዘት ፡ የደረሰው ፡ ይኸው ፡ ነው ፤ ባዕድ-ሠራሹ ፡ *"ሕገ ፡ መንግሥት"* ፥ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ.ን ፡ ይዘት ፡ ለፍጹም ፡ ሙስናና ፡ ፍርሰት ፡ ዳርጎታል ።

እንግዲህ ፥ ለውጡ ፡ እስረኞችን ፡ በመፍታትና ፡ ጕልቻን ፡ በመለዋወጥ ፡ ተዠምሮ ፡ ይዘቱን ፡ በማሸጋገር ፡ ቢቀጥል ፥ አደጋው ፡ ካገሪቱ ፡ በፍጹም ፡ እንዳልተወገደ ፡ እናረጋግጣለን ። በኀላፊነት ፡ ያሉ ፡ ሰዎችም ፡ ኾኑ ፡ ድርጅቶች ፡ ይህን ፡ ልብ ፡ ይበሉ ፦ *የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፡ ይዘት ፡ መቅኖ ፡ የለውም* ። ለዚህ ፡ ነው ፥ ከመደርመሱና ፡ ሀገርንና ፡ ሕዝብን ፡ ከመጕዳቱ ፡ በፊት ፥ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፡ ይዘት ፡ በዘዴ ፡ መወገድ ፡ አለበት ፡ የምንለው ። ይህን ፡ ሥራ ፡ ከመላ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ አንድነታዊ ፡ አካል ፡ በቀር ፡ ማንም ፡ አያገምረውምና ፥ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ አንድነታዊ ፡ አካል ፡ በፍጥነት ፡ መሠራትና ፡ መደርጀት ፡ አለበት ።

*ሥ.መ.* ፤ *ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ መኾኑ ፡ ነውን ፧*

**ወ.ነ.** ፤ አዎን! ፡ ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ ነው ። ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ የመላ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ አንድነታዊ ፡ አካል ፡ ነው ፤ *"ፓርቲ"* ፡ አይደለም ። ኢትዮጵያዊ ፡ ኹሉ ፡ በሀገራዊነቱ ፡ የኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ የመብት ፡ አባል ፡ ነው ። ሀገራዊነታቸውን ፡ እስካልቀየሩ ፡ ድረስ ፥ ይህ ፡ *"ኤርትራውያንንም"* ፡ ይጨምራል ። የግንጠላው ፡ ሕዝባዊ ፡ ፈረዳ ፡ (*"ሬፌራንዶም"*) ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ ነበር ። የክፍለ ፡ ሀገሩ ፡ ነዋሪ ፥ ትላንት ፡ ፈንጂን ፡ እየተራመደ ፥ ዛሬ ፡ ደግሞ ፡ ኬላን ፡ እየሰበረ ፡ ወደ ፡ መኻል ፡ ሀገሩ ፡ ሲመለስ ፥ የመገንጠሉ ፡ ነገር ፡ ትላንት ፡ ሕጋዊ ፡ እንዳልነበረ ፡ ኹሉ ፥ ዛሬ ፡ ደግሞ ፡ በገቢር ፡ ተሽሯል ። ከእንግዲህ ፥ መላው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ (የባሕር ፡ ምድርን ፡ ነዋሪ ፡ ጨምሮ) ፡ እግዚእናውን ፡ ለብሶ ፥ ሕገ ፡ መንግሥቱን ፡ ሠርቶ ፥ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ መንግሥቱን ፡ ማቆም ፡ ይችላል ።

ሱዳን ፣ ደቡብ ፡ ሱዳን ፣ ኬንያ ፣ ሶማልያና ፡ ጂቡቲ ፥ ጎረቤት ፡ ሀገሮች ፡ በመኾናቸው ፥ ታሪካዊ ፡ አንድነታቸው ፣ የወደ ፡ ፊት ፡ ዕጣ ፡ ፈንታቸውም ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ጋራ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ ኢትዮጵያ ፡ ዐዲሱን ፡ ሕገ ፡ መንግሥቷን ፡ በምትሠራበት ፡ ወቅት ፥ ከተመልካችነት ፡ እስከ ፡ ፍጹም ፡ ተሳታፊነት ፡ በሚጠብቅ ፡ ምስትግባር ፡ ቢስተናገዱ ፡ ይጠቅማል ፡ ባይ ፡ ነኝ ።


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።

በተለይ ፡ ሶማልያና ፡ ጂቡቲ ፥ የቅኝ ፡ ገዢዎች ፡ የቀድሞ ፡ የመነጠል ፡ ድርጊት ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ለይቶ ፡ አልለያቸውምና ፥ በዚህ ፡ አጋጣሚ ፡ ዳግም ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ጋራ ፡ የሚዋሐዱበትን ፡ ዕድል ፡ እንዲያገኙ ፥ በሩ ፡ ሊከፈትላቸው ፡ ይገባል ። ዛሬ ፡ ባሕር ፡ ምድሬዎች ፡ ሰተት ፡ ብለው ፡ ወደ ፡ መኻል ፡ አገር ፡ እንደተመለሱ ፡ ኹሉ ፥ በቅርብ ፡ ቀን ፡ ደግሞ ፥ የሶማልያ ፡ ወገኖቻችን ፡ እንዲሁ ፡ አገሬነታቸው ፡ እየሳባቸው ፥ እጅግ ፡ በላቀ ፡ ብዛት ፡ ወደ ፡ መኻል ፡ አገር ፡ ሰተት ፡ ብለው ፡ መግባታቸው ፡ አይቀርም ።

ወደ ፡ ጉዳያችን ፡ ልመለስና ፥ የኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ ዐላማ ፡ አንድና ፡ አንድ ፡ ብቻ ፡ ነው ፦ *መላውን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ በሥልጡንሕዝብና ፡ ርትዕ ፡ መሠረትነት ፡ አዋሕዶ ፥ እግዚእናውን ፡ ማስከበር ፡ ነው ።* የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ እግዚእና ፡ የሚከበረውም ፥ ሕዝቡ ፥ መላ ፡ ሀገሩን ፡ ተቈጣጥሮ ፥ በፍጹም ፡ ነጻ ፡ ምርጫ ፡ በሚሠይመው ፡ ሀገራዊ ፡ ከዋኝ ፡ ጉባኤው ፡ አማካይነት ፥ ዐዲሱን ፡ ሕገ ፡ መንግሥቱን ፡ ሲያረቅና ፡ በሕዝባዊ ፡ ፈረዳ ፡ ሲያጸድቀው ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ ይህኑ ፡ ለመሥራት ፡ ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ ሀገራዊ ፡ ጥሪውን ፡ ያስተላልፋል ። የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ አዎንታዊ ፡ መልሱን ፡ እንደሚሰጠው ፡ እናምናለን ። ባንድ ፡ ቀን ፡ ይከናወናል ፡ የሚል ፡ ሒሳብ ፡ የለንም ፤ ብዙ ፡ ሥራን ፣ ብዙ ፡ ትግልንና ፡ ብዙ ፡ መሥዋዕትነትን ፡ ገና ፡ ይጠይቃል ።

ጠቅላላው ፡ ሥራ ፡ በመላው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፣ ለመላው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ የሚሠራ ፡ እንጂ ፥ ማንም ፡ ሌላ ፡ ባለመብት ፡ የለም ። በተለይ ፡ የስያሳ ፡ ቡድኖች ፡ ወይም ፡ የ"ፖለቲካ ፡ ፓርቲዎች" ፥ በጅምላም ፡ ኾነ ፡ በተናጠል ፥ ከኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ውክልናን ፡ ሳያገኙ ፥ ሕገ ፡ መንግሥትን ፡ ለማርቀቅም ፡ ኾነ ፡ ለማጽደቅ ፡ ምንም ፡ መብት ፡ የላቸውም ። የስያሳ ፡ ቡድኖች ፡ ሥራ ፡ የሚዠምረው ፥ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ሕገ ፡ መንግሥቱን ፡ ሠርቶ ፡ ካጸደቀው ፡ በኋላ ፥ ዐዲሱ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ በሚፈቅደው ፡ አገባብ ፥ በየጊዜው ፡ በሚደረግ ፡ ምርጫ ፡ ተጫርተውና ፡ አሸንፈው ፥ ለተወሰነላቸው ፡ የሥልጣን ፡ ዘመን ፡ አስተዳደሩን ፡ መምራት ፡ ሲዠምሩ ፡ ነው ። ለጊዜው ፡ ግን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ገና ፡ ሕገ ፡ መንግሥቱን ፡ አልሠራም ። ወደ ፡ ፊት ፡ የሚሠራው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ደግሞ ፡ የስያሳ ፡ ቡድኖችን ፡ "ይፈቅድ ፡ / ፡ አይፈቅድ" ፡ ገና ፡ የታወቀ ፡ ነገር ፡ የለም ። የስያሳ ፡ ቡድኖች ፡ ካኹኑ ፡ መደራጀትንና ፡ መዘጋጀትን ፡ የሚከለክላቸው ፡ የለም ፥ አይኖርምም ፤ በሕዝቡ ፡ ምትክ ፥ የኢትዮጵያን ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ "እንሥራለት" ፡ ለማለት ፡ ግን ፡ አንዳቸውም ፡ ይደፍሩ ፡ አይመስለኝም ፤ ምክንያቱም ፥ ይህ ፡ የመላ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ የእግዚእናው ፡ መብቱ ፡ ነው ፤ የተቀደሰ ፡ መብቱ ፡ ነው ፤ ማንም ፡ ሌላ ፡ አያዝበትም ። "እንሥራለት" ፡ የሚሉ ፡ ወገኖች ፡ ቢኖሩ ፥ ይህ ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ዐምባ ፡ ገነን ፡ ሥርዐት ፡ የሚመራ ፣ ሀገርንም ፡ ለውጭ ፡ ኀይሎች ፡ የሚያጋልጥ ፡ ይኾናል ፤ ሐሳቡን ፡ የሚያንሸረሽሩ ፡ ቢኖሩ ፥ ካኹኑ ፡ ርግፍ ፡ አድርገው ፡ እንዲተዉት ፡ በጥብቅ ፡ እናሳስባለን ። ይልቁኑ ፥ የስያሳ ፡ ቡድኖችና ፡ ሥሉጣን ፡ ማኅበሮች ፡ ("ሲቪክ ፡ ማኅበሮች") ፡ ኹሉ ፥ በተለይ ፡ አባሎቻቸውና ፡ ተባባሪዎቻቸው ፥ በሀገራዊነታቸው ፥ ይህን ፡ የሕዝብ ፡ አንድነታዊ ፡ አካል ፡ ለማጐልበት ፡ እንዲያብሩለት ፡ በዚህ ፡ አጋጣሚ ፡ ጥሪያችንን ፡ እናሰማለን ።

የሕዝቡ ፡ አንድነት ፡ በርትዕ ፡ መሠረትና ፡ በርትዕ ፡ መሠረት ፡ ብቻ ፡ የሚገኝ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ የሥልጡንሕዝብናን ፡ ወይም ፡ የኢትዮጵያዊ ፡ "ዴምክራሲ"ን ፡ ርትዕ ፡ ላንድነታችን ፡ መሠረት ፡ መርጦ ፡ ይዟል ፤ የኢትዮጵያን ፡ ሕዝብ ፡ ለማስተባበር ፡ የተሻለ ፡ መሠረት ፡ ይገኝ ፡ አይመስለንም ።

***ሥ.መ.*** ፤ *ይህ ፡ የገለጹልን ፡ ዐቅድ ፥ በገቢር ፡ እንዴት ፡ ይከናወን ፡ ይመስልዎአል* ፧

**ወ.ነ.** ፤ ጥሩ ፡ ጥያቄ ፡ ነው ። ከዚህ ፡ በፊት ፥ በ 1983 ፡ ዓ.ም. ፥ ያሜሪካ ፡ መንግሥት ፡ የለንደኑን ፡ የዕርቅ ፡ ጉባኤ ፡ በሽምጋይነት ፡ ሲጠራ ፥ ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ "የዕርቅ ፡ ሐሳብ ፡ ማስተካከያ ፡ ነጥቦች" ፡ በሚል ፡ ርእስ ፥ በሊየተና ፡ ዤኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ ሊቀ ፡ መንበርነት ፡ ያዘጋጀውን ፡ ሰነድ ፡ በማማረጫነት ፡ ለተደራዳሪዎቹና ፡ ለራሱ ፡ ለሽምጋዩ ፡ ያሜሪካ ፡ መንግሥት ፡ አቅርቦት ፡ ነበር ።

ባለመታደል ፥ ያሜሪካ ፡ መንግሥት ፡ አስቀድሞ ፡ ያደራልን ፡ ሸር ፡ ኖሮ ፥ ድርድሩ ፡ ገና ፡ ሳይዠመር ፡ ተጨናግፎ ፥ አገሪቱን ፡ ለከፋ ፡ ጭቈና ፣ ብዝበዛና ፡ ግንጠላ ፡ ዳረገብን ። ይህን ፡ ክዳትና ፡ ይህን ፡ ሸር ፡ ታሪክ ፡ አይረሳቸውም ።

ዛሬ ፥ ጊዜው ፡ ከመለወጡ ፡ በቀር ፥ የኢትዮጵያ ፡ ኹኔታ ፡ አኹንም ፡ የሽግግርን ፡ ወቅት ፡ የሚጠይቅ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ እላይ ፡ የጠቀስኹት ፡ ሰነድ ፡ ለዛሬው ፡ የሽግግር ፡ ወቅትም ፡ ጠቃሚዎችና ፡ መፍቻዎች ፡ የሚኾኑ ፡ ሐሳቦች ፡ አሉበት ። በርሱ ፡ መሠረት ፡ ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ ዐዲስ ፡


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።

የሽግግር ፡ ሰነድን ፡ አሰናድቷል ። መሠረታዊ ፡ ሰነዳችንን ፡ የማሻሻል ፡ ቀዳሚ ፡ ሥራችንን ፡ እንዳጠናቀቅን ፥ ቀጣዩ ፡ ሥራችን ፡ የሽግግር ፡ ዐቅዳችንን ፡ የሚገልጸውን ፡ ሰነድ ፡ ለመላው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፣ ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፡ ይዘትና ፡ ለሚመለከታቸው ፡ ኹሉ ፡ ማስታወቅ ፡ ይኾናል ። ዞሮ ፡ ዞሮ ፥ ሥራው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ያንድነቱ ፡ ነው ፤ የኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ ድርሻ ፡ የዐላማ ፡ አንድነትን ፡ መስጠትና ፡ በርሱ ፡ መሠረት ፡ ሕዝባዊ ፡ አንድነታዊ ፡ አካሉን ፡ ደርጅቶ ፡ ዐላማውን ፡ ማሟላት ፡ ይኾናል ። የዐላማ ፡ አንድነት ፡ ያደራጀናል ፤ ድርጅት ፡ ተራውን ፡ ዐላማችንን ፡ ያስፈጽመናል ።

***ሥ.መ.*** ፤ *የውጭ ፡ መንግሥታትስ ፥ ይህን ፡ የሽግግር ፡ ሐሳብ ፡ ይደግፉ ፡ ይመስልዎአልን ፧*

***ወ.ነ.*** ፤ የቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ታሪካችንን ፡ እንደ ፡ መነሻ ፡ የያዝን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ መልሴ ፦ *"አብዛኛዎቹ ፡ ለጕዳዩ ፡ ግዑዛን ፡ ናቸው ፤ ጥቂቶቹ ፡ ግን ፥ በግልጽ ፡ ባይቃወሙትም ፡ ይደግፉት ፡ አይመስለኝም"* ፡ የሚል ፡ ይኾናል ። ዛሬ ፥ የዓለም ፡ ኹኔታ ፡ እጅጉን ፡ ተለውጧል ፤ ባጠቃላይ ፥ አህጉራዊው ፡ ግንኙነት ፡ አደገኛ ፡ ኾኗል ። ወሬ ፡ ቶሎና ፡ በቀላሉ ፡ ይወራኛል ። በትንሿ ፡ የዓለማችን ፡ መንደር ፡ ውስጥ ፡ የሚፈነዳ ፡ ፈንጂ ፡ ቀርቶ ፡ የሚነገር ፡ ቃልም ፡ እንኳ ፡ በዓለም ፡ ስያሳ ፡ ወይም ፡ *"ፖለቲካ"* ፡ ላይ ፡ የማይናቅ ፡ ተጽዕኖ ፡ ይኖረዋል ። አይበለውና ፥ የኢትዮጵያ ፡ ስያሳዊ ፡ ኹኔታ ፡ እየተባባሰ ፡ ኼዶ ፡ ወደለየለት ፡ የሥልጣን ፡ ጦርነት ፡ ቢያመራ ፥ ያፍሪቃ ፡ ቀንድና ፡ መካከለኛው ፡ ምሥራቅ ፥ እባሰ ፡ ብጥብጥ ፡ ውስጥ ፡ ገብተው ፥ ስደተኞቻቸው ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ባልታየ ፡ የፍልሰት ፡ ማዕበል ፡ በተለይ ፡ ወደ ፡ ምዕራቡ ፡ ዓለም ፡ ሊፈልሱ ፡ ይገደዳሉ ። ይህ ፡ ቢደርስ ፡ ደግሞ ፡ ባውሮፓ ፡ ኅብረት ፡ ሀልውና ፡ ላይ ፡ የ*"ይምት ፡ በቃ"* ፡ ብይንን ፡ እንደ ፡ መበየን ፡ ያለ ፡ ከባድ ፡ አደጋ ፡ ይኾናል ።

ትላንት ፥ አንዳንድ ፡ ምዕራባውያን ፡ መንግሥታት ፡ የኤርትራን ፡ ከኢትዮጵያ ፡ መገንጠል ፡ እንዲያ ፡ ሲደግፉ ፡ ቈይተው ፥ በመጨረሻ ፥ ኢትዮጵያን ፡ የባሕር ፡ በሯን ፡ በማሳጣታቸው ፡ ረክተው ፡ ነበር ። ዳሩ ፡ ግን ፥ ይህ ፡ ግፍ ፡ ከአካባቢው ፡ ዐልፎ ፡ ለራሳቸውም ፡ መዘዝ ፡ እንደሚኖረው ፡ አላስተዋሉም ። ኹሉንም ፡ ነገር ፡ ከእናት ፡ ሀገራቸው ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሊያገኙ ፡ ሲገባቸው ፥ በመገንጠላቸው ፡ ምክንያት ፡ መትረፈያቸውን ፡ ዐጥተው ፥ ካ1.5 ፡ ሚልዮን ፡ ያላነሱ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ - ፡ ኤርትራውያን ፡ በኤርትራ ፡ ዐቅም ፡ ብቻ ፡ ተመግበው ፡ መኖር ፡ ስላቃታቸው ፥ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ መመለሻው ፡ በር ፡ ቢዘጋባቸው ፥ ወደ ፡ ቀረው ፡ ዓለም ፡ ተሰደዱ ። ብዙዎቹ ፡ አውሮፓ ፡ ድረስ ፡ ዘልቀው ፡ የስደተኛውን ፡ ቍጥር ፡ አባዝተውት ፥ እንደ ፡ ብሪታንያ ፡ ባሉ ፡ ሀገሮች ፡ *"መጤዎች ፡ ወረሩን ፤ ዳር ፡ ድንበራችንን ፡ እንከልክል"* ፡ የሚለውን ፡ ድምፅ ፡ ገንታ ፡ አድርገው ፡ ማሰማትም ፡ ዠመሩ ። ከዚህም ፡ ዐልፈው ፥ አንድ ፡ ፊቱን ፡ ከአውሮፓ ፡ ኅብረት ፡ የመገንጠልን ፡ ከባድ ፡ ውሳኔ ፡ በ2008 ፡ ዓ.ም. ፡ በ*"ብሬክሲት"* ፡ ሕዝባዊ ፡ ፈረዳ ፡ ወስነው ፡ በገቢር ፡ ተገንጠሉ ፤ በዚህ ፡ ረገድ ፥ ብሪታንያ ፡ የመዠመሪያዋ ፡ ጕዳተኛ ፡ ኾናለች ። ሌሎችም ፡ ወደዚሁ ፡ አዝማሚያ ፡ ዘንበል ፡ ሊሉ ፡ ተቃርበዋል ። ይህ ፡ ጕዳይ ፡ ያውሮፓ ፡ ኅብረት ፡ ተቋማትን ፡ ከመሠረታቸው ፡ ሊያናጋ ፡ ይችላልና ፥ አውሮፓውያን ፥ ከንግዲህ ፥ ሰላምን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ማስፈን ፡ ግዴታ ፡ ይኾንባቸዋል ። ምናልባት ፡ ግን ፥ ኢትዮጵያውያን ፡ የምንፈልገውን ፡ ዐይነት ፡ ሰላም ፥ ማለት ፥ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ እግዚእናውን ፡ የሚያስከብርበትን ፣ ዐዲሱን ፡ ሕገ ፡ መንግሥቱን ፡ ሠርቶ ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ መንግሥቱን ፡ የሚያቆምበትን ፡ ሰላም ፡ አኹንም ፡ አይመኙልን ፡ ይኾናል ። ይሄ ፡ ግን ፡ ብዙ ፡ አያስኬዳቸውም ፤ ምክንያቱም ፡ ዛሬ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ነቅቷል ። ለመርዳት ፡ ቢፈቅዱ ፥ የሕዝቡ ፡ አንድነት ፡ በሚያመለክታቸው ፡ ዐይነትና ፡ አገባብ ፡ ይርዱት ፤ ይህን ፡ ማድረግ ፡ ባይፈቅዱ ፡ ግን ፥ አደጋው ፡ በነርሱም ፡ ላይ ፡ ነውና ፥ ያስቡበት ። ዋናው ፡ ጥያቄ ፦ *ያሜሪካ ፡ መንግሥት ፡ ካውሮፓ ፡ ኅብረት ፡ ደኅንነትና ፡ ከራሱ ፡ የምልክ ፡ ግንባታ ፡ ("ኤምፓየር ፡ ብዊልዲንግ") ፡ የትኛው ፡ ይበልጥበት ፡ ይኾን ፧* የሚለው ፡ ነው ፤ ለርሱ ፡ መልስ ፡ የለኝም ።

ያፍሪቃ ፡ ቀንድና ፡ የመካከለኛው ፡ ምሥራቅ ፡ ሀገሮች ፡ ደግሞ ፥ ራሳቸው ፡ ስለተነዋወጡ ፥ ሰላማቸውን ፡ ከመቼውም ፡ የበለጠ ፡ ሣሥተውለታል ፤ ዐልፎ ፡ ኢትዮጵያን ፡ የሚያበጣብጡበት ፡ ዐቅምም ፡ ፋታም ፡ ፍላጎትም ፡ ምክንያትም ፡ የሚኖራቸው ፡ አይመስልም ።

ዛሬ ፥ ኹኔታው ፡ በጠቅላላው ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ አመችቷል ። በመዠመሪያ ፡ ደረጃ ፥ የዓለም ፡ ሕዝባዊ ፡ ስሜት ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ጋራ ፡ ይቆማል ። የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ አንድነታዊ ፡ አካሉን ፡ አጠናክሮና ፡ አደራጅቶ ፥ ሀገሩን ፡ መልሶ ፡ እጁ ፡ አግብቶ ፡ እግዚእናውን ፡ እሚያስከብርበት ፡ ደረጃ ፡ ሲደርስ ፡ ደግሞ ፥ ብዙ ፡ *"ወዳጆች ፡ መንግሥታትን"* ፡ በጋራ ፡ ጥቅም ፡ ዕዛብ ፡ መያዝ ፡ ይችላል ። ሥራውን ፡


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።

ዠምሮታል ፤ ባንጻራዊ ፡ ፍጥነት ፡ እንደሚያከናውነው ፡ አምናለኹ ።

መደጋገም ፡ አይኹንብኝና ፥ ከኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፡ ይዘት ፡ ጋራ ፡ በዐቅዳዊ ፡ ጥቅም ፡ የተቈራኙ ፡ የውጭ ፡ ኀይሎች ፥ ሥርዐቱ ፡ ብዙ ፡ ቢንቀነቅባቸው ፡ አይወዱም ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ብቻ ፥ ያዲሱ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ሥራ ፡ ዐልጋ ፡ ባልጋ ፡ አይኾንልንም ፤ ገና ፡ ብዙ ፡ መሰናክሎች ፡ ይደቀኑብናል ።

ኾነም ፡ አልኾነ ፥ ከንግዲህ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ የማንንም ፡ ጣልቃ ፡ ገብነት ፡ አይታገሥም ። ከራሱና ፡ ከሚተማመንበት ፡ አምላኩ ፡ ሌላ ፡ የማንንም ፡ ሽምግልናም ፡ ኾነ ፡ ሞግዚትነት ፡ አይቀበልም ። ትግሉ ፡ የሚጠይቀውን ፡ መሥዋዕትነትም ፡ አለማመንታት ፡ ይከፍላል ።

*ሥ.መ.* ፤ *የኢትዮጵያን ፡ ስያሳዊ ፡ ኹኔታና ፡ የወደ ፡ ፊት ፡ አዝማሚያውን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ወገኖች ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ መንገድ ፡ ያይዋቸዋል ፤ በተለይ ፥ የሚተነትኑባቸው ፡ የስያሳ ፡ ግሶች ፡ ወይም ፡ ቃላት ፡ በትርጕም ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ ይጣረሳሉ ። ይህ ፡ ኹኔታ ፡ ለሀገራዊው ፡ ንግግርና ፡ ስምምነት ፡ መሰናክል ፡ አይኾንምን ፧*

**ወ.ነ.** ፤ እንዴታ! ፡ ይኾናል ፡ እንጂ! ፡ የቃላት ፡ መጣረስ ፡ ትልቅ ፡ መሰናክል ፡ ኾኖ ፡ ሲያስቸግረን ፡ ኖሯል ፤ የሐሳብ ፡ መጣረሱ ፡ ከቃላቱ ፡ ትርጕም ፡ መጣረስ ፡ ይመነጫል ። *"ዐማርኛን ፡ ማድከም"* ፡ አንዱ ፡ ያጥቂዎቻችን ፡ ቋሚ ፡ ስልት ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ በቀላሉ ፡ የምናስጥላቸው ፡ አይኾንም ። ዋና ፡ ዋናዎቹ ፡ የስያሳ ፡ ግሶቻችን ፥ ኾነ ፡ ተብሎ ፥ በትርጕም ፡ ተጣርሰዋል ። ለምሳሌ ፥ ዋናው ፡ የምንታገልለት ፡ ዐላማ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ *"እግዚእና"* ፡ ወይም ፡ ገገርነት ፡ (*"sovereignty | souveraineté"*) ፡ መከበር ፡ ጕዳይ ፡ ነው ። ታዲያ ፥ *"እግዚእና"* ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ *"ሉዓላዊነት"* ፡ ሲሉ ፡ እንሰማለን ። *"ሉዓላዊነት"* ፡ ማለት ፡ ግን ፡ *"supremacy | suprématie"* ፡ እንጂ ፡ *"sovereignty"* ፡ ማለት ፡ አይደለም ።

ታዲያ ፥ *"sovereignty | souveraineté"*ን ፡ "ሉዓላዊነት" ፡ ካሉት ፥ *"supremacy | suprématie"*ን ፡ ምን ፡ ሊሉት ፡ ይኾን ፧

እንደዚሁ ፥ *"ብሔር"* ፡ ምድር ፡ ማለት ፡ ሳለ ፥ *"ውልደት"* ፡ (ወይም ፡ *"nation"*) ፡ ለማለት ፡ አውለውታል ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በግእዝ ፡ "ብሔረ" ፡ ማለት ፡ መደረ ፣ ሰፋ ፣ ተንጣለለ ፡ ማለት ፡ ነው ።

ብዙዎች ፡ ሌሎች ፡ ቃላትም ፡ አለትርጕማቸው ፡ ውለዋል ። እስከዚህ ፡ ድረስ ፡ ባዝነናል ፤ ... ፡ የምናስበው ፡ ሌላ ፥ ... ፡ የምንናገረው ፡ ሌላ ። የቃላቱን ፡ ትርጕም ፡ በማስተካከል ፡ ሥራችንን ፡ ልንዠምር ፡ ይገባል ።

ሀገራዊ ፡ ቋንቋችን ፡ ዐማርኛ ፡ የሚመግበው ፡ መንግሥት ፡ ዐጥቶ ፡ ለብዙ ፡ ዘመን ፡ ተቸግሯል ፤ አኹን ፡ እባለቤቱ ፡ እኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ እጅ ፡ ተመልሶ ፡ ገብቷልና ፥ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ እያስተካከለ ፡ ይሰጅበታል ፥ ያጣውን ፡ መንግሥቱንም ፡ ይመሠርትበታል ። እግዚአብሔር ፡ ይመስገን ፥ ዛሬ ፡ ደግሞ ፡ እንደ ፡ *"ዐውደ ፡ ቀለም"* ፡ ያለ ፡ የቃላትና ፡ የፊደል ፡ ማረሚያ ፡ መሳሊያ ፡ (*"software"*) ፡ ተገኝቶ ፥ ሥራው ፡ ቀሎለታል ። በተለይ ፡ ከ*"አብዮቱ"* ፡ ወዲህ ፡ በሀገራዊ ፡ ቋንቋችን ፡ ባማርኛ ፡ ውስጥ ፡ የታዩት ፡ የቃላት ፡ ትርጕም ፡ ስሕተቶች ፡ አብዛኛዎቹ ፡ በ"ዐውደ ፡ ቀለም" ፡ ታርመዋል ። መሳሊያው ፡ ከ ፦

www.awdeqelem.net

በነጻ ፡ ይቀዳል ። በመላ ፡ ኢትዮጵያና ፡ በመላ ፡ ዓለም ፡ በፍጥነት ፡ መሠራጨትም ፡ ዠምሯል ።

በሀገራዊው ፡ ንግግር ፡ ረገድ ፥ ከዚህም ፡ የባሰ ፡ አደጋ ፡ አለብን ። ኢትዮጵያ ፡ ጥንታዊት ፡ ሥልጣኔ ፡ መኾኗን ፥ የተሟላ ፡ የግዛት ፡ ሥርዐትና ፡ የዳበረ ፡ ታሪክ ፡ ያላት ፡ ሀገር ፡ መኾኗን ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ትውልዱ ፡ የዘነጋው ፡ ይመስላል ። ታሪካችንን ፡ ንቀን ፡ አለዚያም ፡ ክደን ፡ ከባዶ ፡ እንድንዠምር ፡ የሚሰብኩን ፡ የ*"ንትልዮሽ"* ፡ ወይም ፡ የ*"nihilism"* ፡ ኀይሎች ፡ አሉ ። እነሱንም ፡ መታገል ፡ አለብን ። ያስከበሩንና ፡ አንድ ፡ ያደረጉን ፡ ጥንታውያን ፡ ሥልጣኔያችንና ፡ ታሪካችን ፡ እንዲነወሩና ፡ እንዲከፋፍሉን ፡ በስልት ፡ ተዘምቶባቸዋል ። ይህንም ፡ ጥቃት ፡ መከላከልና ፡ መመለስ ፡ አለብን ። እንደ ፡ ሥልጡንሕዝብና ፡ መዜንው ፡ ያሉ ፡ ማወራኛዎች ፥ በዚህ ፡ ረገድ ፥ ብዙ ፡ ሥራ ፡ ይጠበቅባቸዋል ።

*ሥ.መ.* ፤ *በመጨረሻ ፥ ለኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ በተለይ ፡ የሚያስተላልፉት ፡ መልእክት ፡ ቢኖር ፥ ዕድሉን ፡ እንስጥዎ ።*

**ወ.ነ.** ፤ እግዚአብሔር ፡ ይስጥልኝ ።

በሀገር ፡ ውስጥም ፡ ከሀገር ፡ ውጭም ፡ የምትገኝ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ሆይ! ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ የተፈራረቁብኽን ፡ የጥፋት ፡ አደጋዎች ፡ ኹሉ ፥ በጥንታዊ ፡ ሥልጣኔኽ ፡ ጸንተኽም ፡ ታግሠኽም ፥


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።

ታግለኽም ፡ አሸንፈኽም ፥ እንሆ ፡ ዛሬ ፥ የወደ ፡ ፊት ፡ ዐዳርኽን ፡ ለመወሰን ፡ በያለኽበት ፡ ተነሥተኻል ። ከዚህ ፡ በፊት ፥ ካንዴም ፡ ኹለት ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፥ ተመሳሳይ ፡ ኹኔታ ፡ እያጋጠመኽ ፥ ባለመታደል ፥ ሳትጠቀምበት ፡ በተንኰለኞች ፡ ዕድሉን ፡ ተነጥቀኻል ። ዛሬም ፡ ይህ ፡ ሊደርስብኽ ፡ አይገባምና ፥ ፈጥነኽ ፡ ሕዝባዊ ፡ አንድነታዊ ፡ አካልኽን ፡ ደርጅተኽ ፥ ሀገራዊ ፡ እግዚእናኽን ፡ ማስከበር ፡ ትችላለኽ ። ይህን ፡ መሠረታዊ ፡ ፍላጎትኽን ፡ በማወቅ ፥ የቀደሙ ፡ ወገኖቻችን ፥ በጥፋት ፡ ሰዓት ፡ ሀገርን ፡ የዋጁበትን ፡ የ"ሥልጡንሕዝብና" ፡ መድኀኒት ፡ አቈይተውልኻል ። *"ያባት ፥ ሞቱን ፡ አይወዱ ፥ ረኛቱን ፡ አይሰዱ"* ፡ እንዲሉ ፥ አንተም ፡ ዛሬ ፡ ልትዋጅበት ፡ ይገባል ።

እንሆ ፥ ሕዝባዊ ፡ አንድነታዊ ፡ አካላችን ፡ የሚቆምበትን ፡ የሥልጡንሕዝብናን ፡ መሠረት ፡ ጥለውልን ፥ በአባልነትኽ ፡ የምታዳብረውን ፡ አንድነታዊ ፡ ሕዝባዊ ፡ አካልኽን ፦

*"የኢትዮጵያውያን ፡ ሀገራዊ ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ አንድነት ፡ – ፡ ኢ.ሀ.ሥ.አ."* ፡ በሚል ፡ ስያሜ ፡ አቁመውልን ፡ ዐልፈዋል ። በርሱ ፡ አንድነታዊ ፡ ሕዝባዊ ፡ አካላችንን ፡ ፈጥነን ፡ እንድናጸናበትና ፥ እግዚእናችንን ፡ አስከብረን ፣ ዐዲሱን ፡ ሕገ ፡ መንግሥታችንን ፡ ሠርተንና ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ መንግሥታችንን ፡ አቁመን ፡ ሀገራችንን ፡ እንድንታደግበት ፥ ያንድነት ፡ ጥሪያችንን ፡ በታላቅ ፡ አክብሮትና ፡ በፍጹም ፡ ሀገር ፡ ፍቅር ፡ እናስተላልፍልኻለን ።

ከኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ አብራክ ፡ የወጣችኹ ፡ የቀድሞና ፡ ያኹን ፡ የጦር ፡ ሰራዊት ፣ የሕግ ፡ አስከባሪና ፡ የጸጥታ ፡ አባላትም ፥ በሀገር ፡ መከላከያ ፡ ክንድነታችኹ ፥ ለዚህ ፡ ለተቀደሰ ፡ ሀገራዊ ፡ ዐላማ ፡ መሳካት ፡ የድርሻችኹን ፡ እንድትወጡ ፥ ያንድነት ፡ ጥሪያችንን ፡ እናስተላልፍላችኋለን ። አስተማማኝ ፡ በምትሉት ፡ መንገድ ፡ ኹሉ ፥ ከኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ ጋራ ፡ ግንኙነታችኹን ፡ ፈጥናችኹ ፡ እንድታጠናክሩ ፡ መልእክታችንን ፡ ከታላቅ ፡ ዐደራ ፡ ጋራ ፡ በሀገር ፡ ፍቅር ፡ እናደርስላችኋለን ።

ከኹሉ ፡ አብልጠን ፡ ደግሞ ፥ የሃይማኖት ፡ አባቶችና ፡ መሪዎች ፥ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ለእግዚእናው ፡ መከበር ፡ በሚያደርገው ፡ ርትዓዊና ፡ ሰላማዊ ፡ ትግሉ ፡ የመንፈስ ፡ ድጋፋችኹ ፡ እንደማይለየው ፡ እየተማመን ፥ በጸሎታችኹ ፡ እንድታስታውሱን ፡ በፍጹም ፡ ትሕትና ፡ እንለምናችኋለን ።

ሥራችንን ፡ እግዚአብሔር ፡ ይባርክልን ፤ ሀገራችን ፡ ኢትዮጵያንም ፡ ይታደግልን ።

**ሥ.መ.** ፤ አቶ ፡ ወሴ ፡ ነጋ ፥ ከልብ ፡ እናመሰግናለን ።

**ወ.ነ.** ፤ እግዚአብሔር ፡ ይስጥልን ❖


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።